
# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም በግለሰብ የገጠማትን ችግርና ለወደፊት መሆን ይኖርባቸዋል ተብለው የሚገመቱ መፍትሄዎችን የሚጠቁም የመጀመሪያ መግለጫ ።



ነሐሴ 1994 ዓ.ም
ለንደን ።

# ማውጫ


| ርዕስ | | ገጽ |
|---|---|---|
| 1.0 | ማሳሰቢያ - - - - - - - - | 3 |
| 2.0 | መግቢያ - - - - - - - - | 3 |
| 3.0 | የቤተክርስቲያን መልእክት - - - - - - - | 4 |
| 4.0 | ቤተክርስቲያን ከብጹዕ አቡነ ዮሐንስ እረፍት በኋላ - - - | 5 |
| 5.0 | ብፁአን ሊቃነ ጳጳሳት በለንደን - - - - - - | 6 |
| 6.0 | ቄስ ብርሃኑ ብስራት አገልጋይ ወይስ ******? - - - - | 8 |
| | 6.1 ክህደታቸውና ካህናትና ምእመናንን ለመከፋፈል ከፈጸሙት፤ - - | 9 |
| | 6.2 በመንፈሳዊ አገልግሎት የፈጠሩት ችግር፤ - - - - - | 12 |
| | 6.3. በገንዘብና በሥልጣን ፍቅር የቤ/ክኗ ሰላም ማናጋታቸው፤ - - - | 12 |
| 7.0 | አጠያያቂ የገንዘብ ወጪዎች - - - - - - - | 14 |
| 8.0 | ቤተክርስቲያን ከዚህ ወዴት? - - - - - - - | 16 |

## 1.0 ማሳሰቢያ

የዚህ ጽሑፍ ዋና አላማ የለንደን ደ/ጽ /ቅ /ማርያም ቤተክርስቲያን ከተመሰረተችበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ ከችግር
ያልተላቀቀች በመሆንዋ ለዚህ ሁሉ ችግር መንስኤ የሆኑትን ዓበይት ነገሮች በትንሹ ለመዳሰስና እንዲሁም ደግሞ በምን አ
ይነት ሁኔታ ስወደፊቱ ከዚህ ችግር ልንላቀቅ እንደምንችል ለመጠቆም ነዉ። እዚህ ዉስጥ የቀረቡት ማስረጃዎች በእሉታ
ወይም የወሬ ወሬ ተሰምተዉ ሳይሆን በሂደቱ መሀከል ያለፍንና በአይናችን ያየነዉ ስለሆን ስለ እዉነተኛነቱ ቀርበን የምናስረ
ዳ መሆኑን ልናረጋግጥ እንወዳለን። የተጻፈዉ አስተያየት ትክክል አይደለም ብለዉ የሚያስቡ ካሉ በሰበካ ጉባኤዉ አማካይ
ነት ስብሰባ እንዲጠራ ቢያደርጉ ሥርዓትን ጠብቆ የሚጠይቅ ካለ መልስ መስጠት ይቻላል። መቼም ቢሆን ምእመናን ከተቀ
ደሰዉ መድረክ ላይ ከእዉነትና ከሰላም የራቀ ሀሳብ ከመስጠት መቆጠብ ይኖርባቸዋል። ከሆነም ቃላት ይምረጡ ፤ ከጎንዎ
የቆመዉ አስቀዳሽ የሚታዘብዎ መሆኑን ይረዱ።

እያንዳዳችን የዚች ቤተክርስቲያን አባላት ይህች ቤተክርስቲያን ካለባት ችግር ነጻ ወጥታ በትክክለኛ መንገድ የምትጓዝበትን
፤ ምእመናን በዚች ቦታ ተገኝተዉ መንፈሳቸዉ ሳይረበሽ የሚገለገሉበትን መንገድ የመፈለግ የዉዴታ ግዴታ አለብን ። ነገር
ግን በይሉኝታ ሰዉ አስቀይም ይሆን ወይም ካህኑ የንስሃ አባቴ ሆነዉ እንዴት እናገራለሁ ማለት ራስን ማታለል ይሆናል። እ
ኛም ከነገ ዛሬ ይስተካከል ይሆን በማለት እግዚአብሔር ለሚመስገንበት ቤት እርሱ በፈቀደልን ሰዓት ሁሉ እየተገኘን በሁሉ
ም ተገቢውን ድጋፍ ሰጥተናል፤ ወደፊትም በስጠ ሥራ ዝግጁ ነን። እርስዎም ይህችን አንብበው ምን ቢደረግ ይሻላል ብለ
ው እንዲያስቡና መፍትሄ እንዲጠቁሙ ለማሳሰብ የተዘጋጀ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱሳችን «ወንድምህም ቢበድልህ ፣ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ዉቀሰዉ። ቢሰማህ ፤ ወንድምህን
ገንዘብ አደረግኸዉ፤ ባይሰማህ ግን በሁለት ወይም በሶስት ምስክር ነገር ሁሉ እንዲጸና ዳግመኛ አንድ ወይም ሁለት ካንተ
ጋር ዉሰድ ፤ እነሱንም ባይሰማ ለቤተክርስቲያን ንገራት ድግሞም ቤተክርስቲያንን ባይሰማት እንደ አረመኔና ቀራጭ ይሁንል
ህ።» ማቴ 18፤ 15-18 ይላል። በዚሁም መሠረት ለዚች ቤተክርስቲያን ሥርአት መፋለስ ምክንያት የሆኑትን ሰዉ በግልም
ሆነ በማህበር ብዙ ጊዜ ተመከረዉ አሻፈረኝ በማለታቸዉና የቤተክርስቲያኗም ችግር ከእለት ወደ እለት እየተባባሰ ስለመጣ
፤ ምእመናን ያዉቁት ዘንድ ይህዉ በጽሑፍ ተዘጋጅቶ ቀርቧል። ስለዚህ ይህን ጽሑፍ ስናነብ ችግሩን እያየን ወደፊት ምን
አይነት መፍትሄ አግኝቶ ወደ ተሻለ መንገድ የሚለወጥበትን እያሰብን ይሁን።

## 2.0 መግቢያ

የደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን በመጀመርያ በለንደን ስትመሰረት በአፍሮ ካረቢያኑ ጥያቄ ነበር። በጥያቄዉ
ም መሠረት በወቅቱ የኢ. ኦ. ተ. ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ የነበሩት ብጹእ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አባ አርጋዊ ወ/ገብር
ኤልን (በኋላ አቡነ ዮሐንስን) ለዚህ ሐዋርያዊ ተልእኮ በ1975 እ.አ.አ. ወደ ኢንግላንድ ላኳቸዉ። አባ አርጋዊ ወደዚህ ከመ
ጡበት ጊዜ አንስቶ አፍሮ ካረቢያኑን በማስተማር ፣በማጥመቅ ፣ መንፈሳዊ አገልግሎታቸዉን ጀመሩ። ይህ በእንዲህ እያለ
ዉሎ አድሮ በቁጥር እያደገ የመጣዉ የኢትዮጵያዉያን ምእመናን ቁጥር የአገልግሎቱ ቋንቋ በእንግሊዝኛ ብቻ ሳይሆን በአ
ማርኛም ጭምር እንዲሆን በማለት ጠይቀዉ ነበር።

ይሁን እንጂ አንዳንድ ምእመናን በፈጠሩት ተንኮል ሁለቱ ማህበረሰቦች ስለተጋጩና አብረዉ በአንድነት መገልገል ስላልቻ
ሉ አባ አረጋዊ ከኢትዮጵያዉያኑ ጋር በመሆን ከአከተን ዴል በ1988 እ.አ.አ ወጥተዉ በቤዝዎተር, ቅዱስ ማቴዎስ ቤተክርስ
ቲያን አንዱ ክፍል ዉስጥ የተለመደዉን ግልጋሎት ቀጠሉ። እ.አ.አ ከ1991 በኋላ ከቀን ወደ ቀን የካህናቱና የምእመናኑ ቁ
ጥር እየጨመረ በመምጣቱ የደብረ ጽዮን ቅ/ማርያም ቤተክርስቲያናችን እንደገና ሰፋ ወዳለ ቦታ፤ በግሪን ፓርክ ወደሚገኘ
ዉ ቤተክርስቲያን፤ ተዛወረች። ከዚያ ጊዜ አንስቶ የምእመናኑ ቁጥር በጣም እየጨመረ መጥቶ ነበር። ይሁን እንጂ ቅዱስ
ፓትርያርኩ ወደ ለንደን ለጉብኝት በመጡበት ወቅት በተነሳዉ ሁካታ፤ ቤተክርስቲያኒቱ አገልግሎት ሳትሰጥ ለሳምንታት እን
ድትዘጋ፣ ምእመናንም እንዲበትኑ ፣ተሰፋ ተጥሎበት የነበረዉም የሰንበት ት/ቤት ለረጅም ጊዜ እንዲቋረጥ ሆኗል።

ዉሎ አድሮ ቤተክርስቲያኒቱ በልጆቿ ጥረት ጉዳዩን አስተካክላ አገልግሎቷን ብትቀጥልም ብዙ ምእመናን በዚያዉ እንደወ
ጡ ቀርተዋል። ይህች ቤተክርስቲያን በዚህ ሀገር ከተመሰረተችበት ጊዜ አንስቶ ብዙ የተፈተነችና ፣ እየተፈተነች ያለች
ነች። ይህ በእንዲህ እያለ ብጹእ አቡነ ዮሐንስ በድንገት እስካሁን መንስኤዉ ባልታወቀ ምክንያት ከመሃከላችን እ.አ.አ
በታህሳስ ወር 1997 በሞት ተለይተዋል። በተለይ አቡነ ዮሐንስ ካረፉ ጊዜ ጀምሮ ቤተክርስቲያኗ በጣም የተፈተነችበት ፤ የ
ብዙዎች ጠንካራነት ፤ ደካማነት እና ምንነት የታየበት ወቅት ነዉ። ሁሉንም በዚህና ወደፊት በሁለተኛና በሶስተኛ በተከታ
ታይ በሚወጡት እትሞች ስለሚቀርቡ በአግባቡ አንብባችሁ የበኩላችሁን አስተዋጽኦ እንድታደርጉ ጥሪ ለማቅረብ የተዘጋጀ
ጽሑፍ ነው። በተጨማሪ፤ የችግሩ ፈጣሪዎች ከሆኑት ጋርም ለመወያየትና መፍትሄ ለመፈለግ ብንሞክር አሻፈረኝ በማለት
ስላስቸገሩ ጉዳዩን በሚገባ የተረዱትም በይሉኝታ፣ ጊዜ እየቆጠሩ፣ ከቀን ብዛት የሚፈታ ስለመሰላቸው ብዙ ሥራ የሚሠራበ
ት ሀገርና ጊዜውም በከንቱ ስለባከነ የህሊና ዳኝነት ሁሉም ይስጥበት ተብሎ የተደከመበት ስለሆነ በሚገባ ተከታተሉት እንላ
ለን።

**አዘጋጅ፤ ከእውነት ማህደር**

## 3.0 የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ከተቀበለችው መልእክት ባጭሩ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ያስተምር በነበረበት ወቅት ከሕግ አዋቂዎች ፈሪሳወያንና ሰዱቃውያን አንዱ ከሕግጋትህ ሁሉ ማንኛይቱ ትእዛዝ ትበልጣለች ብሎ ሲጠይቀው «እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም አሳብህ ውደደው። ሁለተኛይቱ ባልንጀራህን እንደነፍስህ፤ እንደራስህ፤ አድርገህ ውደድ የምትለዋ ናት።' በማለት መልሶለታል። (ማቴ. 22፤37-4) ይህንኑ ሕግ በበለጠ ወንጌላው ቅዱስ ዮሐንስ እንዲህ በማለት ያብራራዋል፤ «እግዚአብሔር ፍቅር ነው ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅምና። እንዲሁም ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ፤ በተቸገረ ጊዜ ባይረዳው ቢያማው ሐሰተኛ ነው። የሚያየው ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርንእንዴት ሊወድ ይችላል? እግዚአብሔርን የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህቺ ትእዛዝ ከእርሱ አለች ይላል።» /1ኛ ዮሐ. ም 4 ፣ 8-1/ ብርሃናተ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መጀመሪያ መልእክቱ ላይ ፍቅር ከሌለን በመላእክት ልሳን እንኳዋን እሰከመናገር ብንችል ከንቱ እንደሆንን ይናገራል።

በሰዎች መካከል ፍቅር እንዳይኖር አዳምን ያሳተ ዲያብሎስ ዛሬም ተንኮሉን አልተወውም። ከነዚህ አሳሳች መንገዶች ዋና ዋናዎቹ፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ በአንድ ጊዜ ለመገዛት መታገል፣ በወንድማማች መካከል ሀሜት፣ አለመተማመንን፣ ተንኮል የመሳሰሉትን መፍጠር ነው። ሀሜት ትልቅ ኃጢአት ለመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ ቦታወች ተገልጿል። ሀሜት ለፍቅር አለመኖር ዋና መንስኤ መሆኑ ጥርጥር የለውም። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ ምእ. 4 ፣ 11 «ወንድሞች ሆይ እርስ በርሳችሁ አትተማሙ ይላል።»

መዋደዳችን ምን መምሰል እንዳለበት ለማስመልከት እግዚአብሔር አምላክ ዓለሙን ሁሉ ስለወደደ ዓለምን ለማዳን አንድያ ልጁን ወደ አለም ላከ። እርሱ ስለኛ ነፍሱን አሳልፎ በመስጠት ፍቅሩን አሳውቆናል። 1ኛ ዮሐ 3፤16 ታዲያ እኛም እንዲሁ ስለሌሎች ወንድሞቻችንን ፍቅር ጥቅም ስንል ሕይወታችንን እንኳዋን መስዋዕት ማድረግ ይገባናል። የዚህ ሁሉ ማሰሪያውና መደምደሚያው እርስ በርሳችን መዋደድ መፋቀር ፣ አንዱ ስለአንዱ ይበልጥ ማሰብ ነው። ለዚህም ነው ጌታ «እኔ እንደወደድኳችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህቺ ናት» ብሎ ያስተማረን።

እንግዲህ የክርስትና መሠረቱ ይህ መሆን ካለበት በተለይ አምላካችንን በፍጹም ፍቅር በአንድ ላይ ሆነን እንድናመልክ በተሰጠችን ቤተክርስቲያን ውስጥ አካሄዳችን እንደኛ አስተሳሰብ ወይንም ፈቃድ ሳይሆን እንደ አምላካችን ቃል መሆን ይኖርበታል። ቃሉን የምናደርግ እንጂ የምናሰማና የምንሰማ ብቻ መሆን አይገባንም። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘጠና ዘጠኙን መላእክቱን ትቶ የጠፋውን አዳምን ሊፈልግ እንደመጣ ሁሉ እኛም በተለያየ ምክንያት ከአፀደ ቤ/ክን ደጃፍ የቀሩትን ወገኖቻችንን የቀሩበትን ምክንያት በመጠየቅ፣በመመካከር፣ በመተራረም ማሰባሰብ እና ተመልሰው የሚመጡበትን መንገድ መፈለግ ይኖርብናል። ቤተክርስቲያን የቂምና የበቀል ቦታ ሳትሆን የተዋህዶ አማኞች ኢትዮጵያውያን እና የክርስትናን እምነት በሚገባ ለተረዱ ሁሉ በፍቅር በአንድነት ሆነው በምስጋና የሚኖሩባት ቤታቸው ነች።

ምናልባት በቤ/ክ አገልጋዮችና ተገልጋዮች መካከል በሚነሳው አለፍ አለፍ ያለ የሃሳብ ልዩነት ቅር የተሰኙ ወገኖች ቢኖሩ ከእነርሱ ጋር ያለንን አለመግባባት በረጋ መንፈስ በቅንነት በመነጋገር፣ በመወያየት አስወግደን በቀሪው ጊዜያችን ንስሐ ገብተን አንድ በመሆን ለመንፈሳዊ ሥራ መፋጠን ይኖርብናል። እንዲሁም የበደለ እንኳን ቢኖር ይቅር መባባል እንደሚገባንም የአምላካችን ቃል ግልጽ አድርጎ ያስረዳናል። ለእምነታችንና ለአንድነታችን ዋና መሠረቱ ፍቅር በመሆኑ እርስ በርሳችን በመዋደድ መጠናከር እንጂ ለጥልና ጭቅጭቅ ቦታ ሊኖረው አይገባም። የአምላካችን ቃልማ ባልጀራችንን ብቻ ሳይሆን ጠላቶቻችንንም ጭምር መውደድ እንዳለብን ይነግረናል።

ነገር ግን ፍቅር በቤተክርስቲያናችን ውስጥ እንዳይሰፍን ሆን ብሎ እንቅፋት ለሚሆኑ (ለሆኑ) ካህናትም ሆነ ምእመናን በንስሐ እስካልተመለሱ ድረስ አምላካችን ለቤቱ ቀናተኛ ነውና ፍርዱ የማይቀር ነው። በፍጹም ሰውነታችን እግዚአብሔርን ልንፈራው ፣አገልጋዮቹን ካህናትንም እንድናከብራቸው ተጽፎአል። (መጽ. ሲራክ 7፤29) ይሁን እንጅ ካህን በመሆን ብቻ ንጽህና ቅድስና ይገኛል ማለት አይደለም። ለዚህም የእግዚአብሔር ነቢይ የሆነው ኤርምያስ ። «የማሰማሪያዬን በጎች ለሚያጠፉና ለሚበትኑ ወዮላቸው! ይላል እግዚአብሔር፤ ...... በጎቼን በትናችኋል ፣ አባራችኋቸውማል አልጎበኛችኋቸውም እነሆ የሥራችሁን ክፋት እጎበኝባችኋለሁ ይላል እግዚአብሔር።» ትን. ኤር ም 23፤1-3 ይህ ማለት ደግሞ ከቤተክርስቲያን ተሰናክለ ውስሚቀሩ ተጠያቂዎች ካህናት ብቻ ናቸው ማለት አይደለም፤ እያንዳንዱም ምእመን ጭምር እንጅ። ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሲያስተምር «በእኔ ከሚያምኑ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን ያሰናከለ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባህር መስጠም ይሻለው ነበር» (ማቴ 18፤5) ያለውን ማስታወስ ይኖርብናል።

ስለዚህ እያንዳዳችን እንደ ሕጉ ልንኖርና ስለሌሎች ወንድሞቻችን መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ ህይወት ልናስብ ፤ በእኛ የተሳሳተ አካሄድ እንዳይሰናከሉ ልንጠነቀቅ ይገባል። ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ «አቤቱ ንፁህ ልብን ፍጠርልኝ፣ የቀናዉንም መንፈስ በውስጤ አድስ» እንዳለዉ እኛም አምላካችን ይህን እንዲያደርገልን በጸሎት ልንጠይቀዉ ይገባል።

## 4.0 የደ/ጽ/ቅ/ማ/ ቤ/ክ ከብጹእ አቡነ ዮሐንስ እረፍት በኋላ

ብጹእ አቡነ ዮሐንስ ካረፉ በኋላ ቤተ ክርስቲያናችን ከአሁን ጀምሮ እንዴት ነው የምትመራው የሚል ጥያቄ ተነስቶ ነበር። ይህን በተመለከተ ለመወያየት በ17-1-98 እ. አ.እ የመጀመሪያው የማህበረ ካህናት ስብሰባ ተደርጎ ነበር። በስብሰባው ላይ ከተነሱት ዋና ዋና ነጥቦች መካከል የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ማን ነው? ወደፊት እንዴት ነው ይህች ቤተክርስቲያን የምትመራው? የሚሉት ነበሩ። ለእነዚህ ጥያቄዎች መልሱን ቀልጠፍ ባለ አነጋገር ቄስ ብርሃኑ ብሥራት እንዲት ወረቀት ከኪሳቸው በማውጣት አቡነ ጳውሎስ በተጠባባቂነት የሾሟቸው መሆኑን የሚያስረዳ ደብዳቤ ለተሰበሰቡት ካህናት ያነባሉ። በመቀጠልም ከካህናቱ መሀከል አንዱ በመገረም ለመሆኑ ይህችን ቤተ ክርስቲያን ለመምራት ችሎታው ወይም ልምዱ አለዎት ወይ? ብሎ ላቀረበላቸው ጥያቄ እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ትውፊትና ፣ እንደ ባሕላችን በእግዚአብሔር እርዳታ፤ ወይም ከሁላችሁ ጋር በመሆን ፣ በመተባበር ሳይሆን በወኑ በማያዉቁት ቋንቋ በእንግሊዘኛ «of course» በማለት ምላሽ ይሰጣሉ።

በጉባኤው የተገኙት ካህናትም ለጊዜው በቅስና የሚያገለግል ሌላ ካህን ባለመኖሩ ፤ ሌላውን ጊዜ ይፍታው በማለት ግለጋሎቱ እንዲቀጥል ተስማሙ። እያደር ግን የቤተክርስቲያኒቷ የአዛዥና ታዛዥ ማንነት ባለመታወቁ በተለያየ መልኩ አገልግሎቱ እየተዳከመ ሲሄድ፤ የሰዓት አለመከበር፣ የጸሎተ ቅዳሴው ባልተሟላ ሁኔታ መካሄድ፣ የሰብከተ ወንጌል መዳከም፣ የፕሮግራም መዛባት፣ ለክርስትናና ለሥርዓተ ተክሊል አገልግሎት የሚመጡ ምእመናን አስፈላጊውን ምክርና ትምህርት አለማግኘት. . . ወዘተ ሲገጥም ጉዳዩ መፍትሄ የሚያስፈልገዉ ሆኖ ቀረበ። ይህ በእንዲህ እንዳለ፤ ቀደም ሲል አቡነ ዮሐንስ በህይወት ሳሉ የካህናት የሥራ ድርሻ ክፍል አገልግሎትን እና የገንዘብ አስተዳደርን አጠቃሎ የያዘ የውስጥ ደንብ እንዲያረቅ ኮሚቴ ተቋቁሞ በአስቸኳይ አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ ታዞ ነበር። ይሁን እንጂ የስራ ግዴታውን በአንዳንድ ምክንያቶች መወጣት ስላልቻለ ሌላ 6 አባለትን የያዘ ኮሚቴ፤ ከምእመናንም ጭምር ተዋቅሮ፤ ለቤተ ክርስቲያኗ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ እንዲያዘጋጅ አደራ ተጣለበት። በዚሁም መሠረት ይህ ኮሚቴ የመጀመሪያውን ረቂቅ በ21-03-98 እ.አ.እ ለማህበረ ካህናት ጉባኤ ለውይይት አቀረበ። ይሁን እንጂ አንዳንድ ካህናትና እና ምእመናን ረቂቅ የውስጥ መተዳደሪያ ደንቡ ወደ አመጨረሻው ሳይደርስ አልቆ እንደወጣና እንደጸደቀ በማስመሰል ወደ ኢትዮጵያ ቤተ ክህነት በመላካቸው በአጋጣሚ ከፍ ያለ አለመግባባት ሲፈጠር ችሏል።

<u>በዚህም የተነሳ ቅዱስ ፓትርያርኩ በፍጥነት ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገ/አማኑኤልን የደ/ጽ/ቅ/ማ/ቤ/ክንን እንዲያስተዳድሩ ወደ ለንደን ላኳቸዉ። ሊቀ ካህናቱም በ 5-4-98 እ.አ.እ በድንገት ቤተ ክርስቲያን ደርሰው በወቅቱ ካህናቱም ሆኑ የሰበካ ጉባኤው በምልአት ሳያውቁትና ሳይረዱት፤ ያለምንም ትውውቅ በገዛ ፈቃዳቸው ቅዳሴውን መርተዋል።</u> ሥርዓተ ቅዳሴውም እንዳበቃ፤ ለሁሉም እንግዳ ደራሽ የሆነውን የእርሳቸውን የአስተዳዳሪነት ሹመትና ፤ የቄስ ብርሃኑን የተጠባባቂነት ሽረት የሚያሳውቀውን ደብዳቤ በእለቱ ለተገኙት ምእመናን አሰምተዋል። በእለቱ የእንግዳውን ተሹሞ መምጣት፣ የተጠባባቂውን መሻር አዋጅ ያስተናገዱት ቄስ ብርሃኑ ብስራት ለምእመናኑ « .....ያው አስተዳዳሪ ስለተላከልን ከዛሬ ጀምሮ የእኔ በተጠባባቂነት በቦታው ላይ መቆየት አብቅቷል። ከአሁን በኋላ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገ/አማኑኤል ናቸው በማለት ሲናገሩ ለውስጥ አዋቂዎች ፤ ምክንያቱ ሀገር ቤት ከቤተ ክህነት በለንደን እየሰጡ ሳለው አገልግሎት በባለቤታቸው እጅ እየተፈረመ የሚከፈላቸው መጠኑ በውል ያልታወቀ ወርሃዊ ደመወዝ እንዳይቀርባቸው ከፍተኛ ስጋት ሰላላቸው መሆኑ ግልጽ ነበር። ይኸውም <u>ከጥቅምና ከሹመት ጋር የተሳሰረ የጠበቀ ግንኙነት</u> እንዳላቸው በግልጽ አመልክቶናል።የሆኖ ሆኖ፤ ሊቀ ካህናት ብርሃኑ በእንዲህ ዓይነት መንፈስ ባህር አቋርጠው መጥተው በእነ ስመአይጠሩ ምክር በመጓዛቸው ችግሩ ወደ እርሳቸው ባልጠበቁት መንገድ ውስጥ ውስጡን እየተንቦገቦገ ቆየና የሰበካ አስተዳድር ጉባኤ አባላት፣ ማህበረ ካህናትና አንዳንድ ምእመናን ተሰባሰበው ወቅቱ (አቢይ ጾም) የጾምና የጸሎት በመሆኑ ስለማንኛውም ነገር ከትንሳኤ በዓል ውጭ ለመነጋገር ወስነው ተለያዩ። የዚህ ጽሁፍ አላማ በዚያን ጊዜ ስለተፈጠረው ችግርና የተወሰዱትን የመፍትሄ ሀሳቦች ለማስገንዘብ ስላልሆነ እዚህ ላይ ለመግታት ተገደናል። ይህን በተመለከተ ማህበረ ካህናቱና ምእመናኑ እንዲያውቁትና እንዲረዱት ከተፈለገ ወደፊት እራሱን የቻለ ሰፊ ጽሁፍ ማቅረብ ይቻላል።

ወደ መነሻው እንመለስና እየተረቀቀና እየተዘጋጀ የነበረው የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ለማህበረ ምእመናንና ካህናት የዳግም ትንሣኤ እለት እ.አ.እ (1998) እንዲቀርብ ተወስኖ ነበር። በዚህ ወቅት ቄስ ብርሃኑ ብስራት ይህ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ከምን እንደደረሰ ከመጠየቅ ቦዝነው አያውቁም ነበር። ይሁን እንጂ ሁላችንም እንደምናስታውሰዉ የዳግም ትንሳኤ እለት ያ ይጠበቅ የነበረው ስብሰባ እንዳይካሄድና በዉይይት ችግሩ እንዳይፈታ በማሰብ፤ በእነ ስምአይጠሩ ምሪት እንግዳው ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ቤተ ክርስቲያኑን ቆልፈው ጠፉ። በዚህ ሥራ ያዘነው መላው ምእመናን በ 2-5-98 እ.አ.እ ቤተ ክርስቲያኑ እንዲከፈት በአንድነት ብርቱ ጥረት ካደረጉ በኋላ ሊቀ ካህናት ብርሃኑ የፈጸሙትን ተግባር እንዳይደግሙት በማሰብ ከነስምአይጠሩ ጋር ተመልሰው ከቤተ ክርስቲያናችን እንዳይደርሱ በማለት በሙሉ ድምጽ በመወሰኑ፤ ዘግተው ከወጡበት ቤተ ክርስቲያን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሳይመለሱ ቀርተዋል። እውነት፣ ሕብረትና አንድነት ምን ማድረግ እንደሚችል በዚያን ቀን ተመስክሯል።

ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ፤ የተጀመረው የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ፍጻሜ ያገኝ ዘንድ በ17- 5-98 እ.አ.እ ከቅዳሴ በኋላ አጠር ያለ መግለጫ ተሰጥቶ የተሻሻለው የውስጥ መተዳደሪያ ረቂቅ ደንብ ለጠቅላላው ጉባኤ አስተያየት እንዲሰጥበትና ታርሞ ጸድቆ የቤተ ክርስቲያኒቷን መብት እንዲያስከብር በውስጧም የሚገኙ አገልጋይ ካህናትና ተገልጋይ ምእመናን መብትና ግዴታቸውን በማያሻማ ሁኔታ ያስገንዝባል ተብሎ ተገምቶ ነበር። ምእመናኑ በረቂቁ ላይ ያላቸውን አስተያየት በተደጋጋሚ በተደረጉ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት፤ ለስብሰባ መምጣት ያልቻሉ ደግሞ በደብዳቤና በስልክ አስተያየታቸውን ሲሰጡበት ሰንብተዋል። <u>ይሁን እንጂ እያደር፣ እየዋለ ብቸኛ አገልጋይ መሆናቸው እየተሰማቸው የመጡት ቄ</u>

ስ ብርሃኑ ብስራት፤ በጊዜው ምእመናኑ ሌላ አማራጭ ካህን ስለሌላቸው እንደፈለጉ በቤተ ክርስቲያኑ ሀብትና ንብረት ማዘዛቸው እንዳይቀር በተለያየ ዘዴ፤ በአስቸኳዋይ እንዲወጣ ይደገፉት የነበረዉን የዉስጥ መተዳደሪያ ድንብ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጸድቆ ወጥቶ በሥራ ላይ እንዳይውል ተቃዉሞ ማሰማት ጀመሩ።

ለመጨረሻ ጊዜ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ በ19-12-98 እ.አ.አ የውስጥ መተዳደሪያ ረቂቅ ደንቡ ለጠቅላላው ጉባኤ በሪፖርት መልክ ቀረበ። በውሳኔው መሠረት ከሪፖርቱ በኋላ ምእመናኑ አስተያየታቸውን ለማከል ሲነሳሱ ቄስ ብርሃኑ ብሥራት ግን በማን አለብኝነት ፈገግ እያሉ የውስጣቸውን ፍላጎት ስለማያሟላ በግላቸው ተቃዉመዋል። በመጨረሻም ታርሞ የቀረበው የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ሲታደል እኝሁ ካህን ቀደም ሲል የታደለዉ ኮፒ ላይ እንዲሻሻል የጠየቁትን ከእሳቸዉ ፍላጎት አኳያ ወጥቶ ባለማግኘታቸዉ በአርቃቂዉ ኮሚቴ አባላት ላይ ዛቻ የተላበሰ ንግግር አሰምተዋል።

በመሠረቱ በሕግ አልመራም የሚል ሥርዓት-አልበኛ ፣ ሕገ-ወጥና እንዲሁም ሌላ ከበስተጀርባ በድብቅ የሚፈልገው ገንዘብ፣ ሥልጣን ፣ ሌላም ጥቅም ያለዉ ነዉ። ይህ የተዘጋጀው የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ በጊዜው ለነበሩ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አባላትም ጭምር በደንብ ተጠርዞ ሲሰጣቸው፤ እነርሱም በአስቸኳይ የሚጸድቅበትን መንገድ እንዲያመቻቹ በማስገንዘብ ነበር። ነገር ግን እስከ አሁን ሁላችንም ባልተረዳነው ምክንያት እንዲሁ የውሃ ሽታ ሆኖ ቀርቷል። ከዚያም በላይ የሚገርመው ነገር እንደዛ ለመላው ምእመናን ከሁለት ሳምንት በኋላ ይጸድቃል ተብሎ ቢነገርም በጣት ከሚቆጠሩ ተቆርቋሪ ምእመናን በስተቀር በአብዛኛው የውስጥ መተዳደሪያ ደንቡ የት ደረሰ? ለምንስ ነው እንደዚያ ተለፍቶበት የማይጸድቀውና የማይሠራበት ብሎ አለመጠየቁ ነው።

የውስጠ ደንብ አርቃቂ ኮሚቴም ሲጠየቅ «ፈሪስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም » እኛ ያለብንን የተመረጥንበትን ኃላፊነት ተወጥተናል ከአሁን በኋላ ግን የቤተ ክርስቲያኗንና የማህበረ ካህናትና ምእመናኑን መብት ማስከበር ያለባችሁ እናንተው ካህናቱና ምእመናን እራሳችሁ ናችሁ በማለት መልስ ሰጥተዋል። መቼም አንድ ህዝብ የሚገባውን መሪ ያገኛል እንዲሉ፤ አሁንም የሚበጀው ሕግና ሥርዓቱ ተዘጋጅቶ፣ ጸድቆና ታውቆ ፣መሪና ተመሪም በአንድነትና በፍቅር ማገልገልና መገልገል ሲቻል ብቻ ሰላም የሚገኝ መሆኑንም ይህ ዘገባ ሳያበክር አያልፍም። ይሁንና አሁን ከ3 ዓመት በኋላ ምእመናንና ካህናት የውስጠ ደንቡን መውጣት ከመቼውም በላይ ሰላመኑበት በአሁኑ ሰዓት ባሉት የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አማካኝነት ከተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች የሕግ አርቃቂዎች ተዋቅረው የውስጠ ደንብ ማርቀቅ ሥራውን እ.አ.አ በግንቦት 2002 ጀምረዋል።

ሆኖም የገበያ ግርግር .......... ያመቻል እንዲሉ፤ የአገልጋይና ተገልጋይ ኃላፊነት ባልታወቀበትና አስተዳዳሪም ሆነ ሐላፊ በሌለበት ቦታ ቄስ ብርሃኑ ብስራት ከጥቂት የመንደር አደጎቻቸውና ከአንዳንድ መሠረታዊ የክርስትና እምነቱን ጠልቀው ካልተረዱ ምእመናን ጋር በጽዋ ስም ማህበር አደራጅተው የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን እንደ ግል ንብረትና ውርስ የኛ ብቻ ናት ሲሉ ማየቱ በጣም ነበር የሚያስገርመው። ቄስ ብርሃኑ ስንት የቤተ ክርስቲያናችን ምሁራን ባሉበት በዚህ ሀገር፤ የራሳቸውን እውቀትና ልምድ ብዙም ሰላላኮራቸው፤ በተለያየ መልክ በሌሎች ካህናት ላይ እያሳደሙ በቤተ ክርስቲያኗ ላይ እራሳቸውን አዛዥ አድርገው ሹመው ከመገኘታቸውም በላይ፤ ይህችን ቤተ ክርስቲያን ካለ እኔ በስተቀር ማንም አይመራትም አለበለዚያ ትዘጋታለች፣ ትከፋፈላለች፣ ሕዝቡን እበትናለሁ... ወዘተ. በማለት ሊቀ ጳጳሳት በተገኙበት ስብሰባ ለይ ሁሉ እስከመናገር የደረሱ እና ጥቅማቸዉ ከተቀነሰ የቤተ ክርስቲያን መፍረስ የሚመርጡ ቄስ ናቸዉ። ይሁዳ ታላቁን የዓለም መድኃኒት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለ30 ብር አሳልፎ እንደሰጠ እንዲሁ፤ ቄስ ብርሃኑም ለገንዘብ ሲሉ ለዚያዉም ለ600 ፓውንድ ምእመናን እንዲከፈሉ፣ እንዲበተኑ፣ ቤ/ክኗ እንድትፈርስ አደርጋለዉ በማለታቸዉ ከእንግዲህ በኋላ በታሪክ የመጀመሪያ ተጠቃሽ ይሆናሉ።

በወቅቱ የነበረው የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ በእርግጥ በእንዲህ ዓይነት የፈተና ወቅት የቤተ ክርስቲያኗን አስተዳደር ለማቃናት ከፍተኛ ሚና መጫወት ይችል ነበር። ነገር ግን ጊዜው ያለፈበት፣ በቁጥር በጣም ያነሰ (ሁለቱ የኮሚቴው አባላት ከእኝሁ ራስ ወዳድ ካህን ጋር ባለመስማማት ስራቸውን በፈቃዳቸው ቢለቁም በቦታቸው ሰው መተካትም ሆነ የሚለቁበትን ምክንያት ለማስረዳት ቀሪው የአስተዳደር ጉባኤ ሰላልፈለገ ዝም ጭጭ ተብሏል።) እንዲሁም ብዙዎቹ የሰበካ ጉባኤ አባላት ከቄሱ ጋር በጣም የተቀራረቡ በመሆናቸዉ ከእንደበታቸው ይህ ቢሆን የሚል ሊወጣ አልቻለም። በእነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች የአስተዳደር ጉባኤው እንዲያው ለወጉ ወይም ለስሙ አለ ይባላል እንጂ ከቦታው አልነበረም።

## 5.0 ብፁእን ሊቃነ ጳጳሳት በለንደን

5.1 ነሐሴ 1998 እ.አ.አ ብፁእ አቡነ ሰላማ ወደ ለንደን ለአገልግሎት ተልከው ለ6 ወር ያህል ቆይተው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል። እኝህ አባት ጥሩ ባህታዊና ጸሎተኛ ነበሩ። ነገር ግን ባለወቂት ጉዳይ ቄስ ብርሃኑ ከሰዎች ጋር እንዳይገናኙ አቤታቸው በማስቀመጥ ሌሎች ወደፊት በቀጣዩ እትም ታሪካቸው ከሚወጣ ጋር በመሆን፤ የተወሰኑ ካህናትና ምእመናንን ችግር ፈጣሪዎች አድርገው በማቅረብ ብዙ መሥራት እንዳይችሉ እንቅፋት ሆነዉባቸዋል። እንዲሁም በቤተ ክርስቲያኗ ገንዘብ ለአውሮፓ ሥራ በማለት የግል አላማ ለነበራቸው አስተርጓሚዎች ጭምር ወጪ ከቤ/ክ ገንዘብ በማድረግ ሲያዞሯቸው ከርመው ያለ አንዳች ፍሬ እኝህ አባት ወደ ሀገራቸው ሊመለሱ ችለዋል። እኝህን የመሰሉ አባት መጥተው ብዙ ሥራ መሥራት ሲቻል፤ እነኝሁ የቤ/ክን ችግር የሆኑ ግለሰቦች፤ በፈጸሙት ድርጊት ሳንጠቀምባቸው መሄዳቸው ሁሉን በእጅጉ አሳዝኗል።

5.2 ታህሳስ 1999 እ.ኢ.አ ብፁእ አቡነ መልከ ጼዴቅ ወደ ለንደን መጥተዉ የመጀመሪያ አገልግሎታቸዉን በሥርዓተ-ቅዳሴ የጀመሩት በ 03. 01.1999 እ.ኢ.አ ነዉ። እኝህም አባት ከመጡበት ጊዜ አንስቶ ምእመናኑን በማስተማር፣ ቤተክርስቲያኒቷ የ ምትጠናከርበትን መንገድ ሲቀይሱ ቆይተዋል። ከፈጸሟቸዉ ዓበይት ተግባራት መሀከል፤

5.2.1) በየሳምንቱ እሁድ የስብከት ዘዴያቸዉን በመጠቀም ስብከተ ወንጌልን በቤተክርስቲያን ማስፋፋታቸዉና በዚህም የተነሳ የምእመናን ቁጥር መጨመሩ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነዉ። በዚያ ማራኪ ትምህርታቸዉና ፣ መልካም ባህርያቸዉ የተመሰጡ ምእመናን ከህጻናት አንስቶ በእድሜ የገፉ አዛዉንት ሳይቀሩ ወደ መኖሪያ ቤታቸዉ በመሄድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ይ ከታተሉ እንደነበር ሁላችን የምናስታዉሰዉ ነዉ።

5.2.2) የሰንበት ት/ቤቱ በአዲስ መልክ እንዲዋቀርና መርሐ-ግብሩ በሰፋ ሁኔታ እንዲካሄድ ማመቻቸታቸዉ፤

5.2.3) ወጣቶች መ/ቅዱስን በደንብ ተምረዉ በዉጭም ሆነ በዉስጥ ማስተማር እንዲችሉ የተምሮ ማስተማር መርሐ-ግብርን በመክፈት አቤታቸዉ ቁጥራቸዉ የበዛ ወጣቶች እየተሰባሰቡ እንዲሳተፉ አድርገዋል። እያደር ቁጥራቸዉ እየተበራከተ በመ ምጣቱም ከቤታቸዉ ቀርቶ በቤተክርስቲያን እንዲሆን ሆኖ እሳቸዉም ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በሁዋላ መርሐ-ግብሩ በዚያ ዉ ቀጥሉአል።ይሁን እንጂ በመጋቢት ወር 2000 እ.ኢ.አ ቄስ ብርሃኑ ብሥራት መርሐ-ግብሩ አስፈላጊ አይደለም በማለት በ ግል ፈቃዳቸዉ ዘግተዉታል። ወጣቶቹ በተምሮ ማስተማር ተምረዉ እኔ የማላውቀውን ቀድመው ካወቁ ከግምት ውስጥ አገ ባለሁ በማለትና ይህን ጠፍ ቦታ የማስተዳድር መሆኔን በዚህ እንኳን ይታወቅልኝ ብሎ ለጥፋት መቸኮል እውነትም ቤ/ክኗን አፈርሳለሁ ያሉት እውነታቸውን ነው ያሰኛል።

ይህ የተምሮ ማስተማር መርሐ-ግብር የተቋቋመዉ ለወጣቶች ብቻ ሳይሆን ለካህናቱም ጭምር ነበር። በዚህም መርሐ-ግብር ላይ ቄስ ብርሃኑ ከሌሎች ዲያቆናት ጋር በመገኘት ትምህርቱን ይከታተሉ እንደነበር ይታወቃል።

አቡነ መልከ ጼዴቅ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ ሳደረጉት መልካም ስራ ምስጋና ሲገባ ለህዝብ ብዙ በደል እንደበደሉ አስመስሎ በአደባባይ ሳይቀር ሲናገሩ፤ እንዲሁም ቀደም ብሎ አስጀምረዉት የነበረዉን ትምህርት ጠቃሚነቱን በመዘንጋት አቡኑን የጎዱ መስሎአቸዉ ትምህርቱ እንዲቋረጥ አድርገዋል። ይህንን መርሐ-ግብር ለመዝጋት ቄስ ብርሃኑ ከቋመጡ ብዙ ቆይተዋል። በጥቅምት ወር 1999 እ.ኢ.አ በተካሄደዉ የካህናት ጉባኤ ላይ የማከሰኞን የተምሮ ማስተማር መርሐ-ግብር አላስ ፈላጊነት ደጋግሞ በማዉሳት የካህናቱን ድጋፍ ለማግኘት በጣም ጓጉተዉ እንደለመዱት ያለ የሌለ ዉሸት በማቅረብ ጉባኤዉ ን ለማሳመን ሲጥሩ ብዙ ትዝብት ላይ ጥሎአቸዋል።ይሁን እንጂ የካህናት ጉባኤዉ የተምሮ ማስተማር መርሐ-ግብሩን ከመ ዝጋት በፊት ችግር ወይም የሚሻሻል ነገር ካለ ሁኔታዉን እንዲያጣራ 4 ካህናትን ወክሎ ከወጣቶቹ ጋር እንዲነጋገር ተወሰነ ። ተወካዮቹም በጉባኤዉ ተገኝተዉ የትምህርቱን ይዘት ካዩ በኋላ ከወጣቶቹ ጋር ዉይይት አካሂደዋል። ከዉይይቱም የተገ ኘዉ ዉጤት እንደሚያሳየዉ ከሆነ ፤ በተወከሉት ካህናት ላይ ወጣቶች ተጨምረዉ በአጠቃላይ በቤተክርስቲያን ዉስጥ የሚካሄደዉን ትምህርት በተዋቀረ መልኩ እንዲሰሩ ተወሰነ። ቄስ ብርሀኑ ደግሞ እንዲዘጋ ቋምጠዉለት የነበረዉ ጉባኤ ለበ ለጠ ሥራ ዝግጅት ጀመረ። የዘወትር ኃሳባቸው ብርሃን ሳይሆን ጨለማ ነውና በድንጋጤ ተያዙ።

ይህ በእንዲህ እያለ በአዲሱ የሰበካ ጉባኤ ምርጫ ወቅት በተፈጠረዉ አለመግባባት ፤ ምእመናንም በየጎራዉ ሲከፋፈሉ፤ በ ቤተክርስቲያን ሁሉንም አገልግሎት በአንድነት ይሰራ የነበረዉ የካህናት ጉባኤ የቤ/ክኗ በር እየተዘጋበት እንዳይሰበሰብ ሲታ ገድ፤ ይህ አጋጣሚ ለቄስ ብርሃኑ ጥሩ እድል ፈጥሮላቸዋል። በዚህም መሠረት መጋቢት ወር 2000 እ.ኢ.አ እሁድ ቄስ ብር ሃኑ ለወጣቶች «የተምሮ ማስተማር መርሐ-ግብሩን ከእንግዲህ ወዲያ ቤ/ክኑን እንደማይከፍቱና ፤ ለዚህም ምንም ምክንያት መስጠት እንደማያስፈልጋቸዉ በኃይለ ቃል ፤በግለፍተኝነትና ፤ በቁጣ ተናግረዋቸዉ» ትምህርቱን ዘግተዉታል። በዚያም ት ምህርቱን ይከታተሉ ከነበሩት አንዷ ወጣት «የሚዘጋበት ምክንያቱ ምንድን ነዉ ?» ብላ ስጠየቀችዉ ፤ ቄስ ብርሃኑ የመለ ሱላት «ካንቺ ጋር ዝቅ ብዬ ለማዉራት ክብሬ አይፈቅድልኝም ብለዋል።» መቼም ስደት ለወሬ ያመች የለ!!!!!! እንደ መ / ቅዱሱ ቃል ቢሆንማ ታናናሾቻቸዉን ሁሉ ሳይቀር ማክበር ይገባቸዉ ነበር።

በዚህ መርሐ-ግብር መዘጋት የተከፉ ወጣቶች አጥጋቢ መልስ መሰጠት አለበት ብለዉ በተደጋጋሚ ላቀረቡት ጥያቄ የተሰጣ ቸዉ መልስ « የሚመጡት 2/3 ልጆች ናቸዉ፤ ለነዚህ ደግሞ ብዬ ወርቃማዉን ጊዜዬን አላቃጥልም...» ነበር። ከዚያም እ ልፈዉ እዚያ ለይ የሚመጡት ልጆች ትምህርት ሳይሆን የሚያወሩት ሌላ ነዉ በማለት የተለመደ የቅጥፈት ሰበባቸዉን ሰጥ ተዋል። በዚህ መልስ ያልረካዉ አንዱ ወጣት በመ/ቅዱሱ ላይ «አንድም ሶስትም ሆናችሁ በተገኛችሁበት እኔ እገኛለሁ ይ ላል......» እርስዎስ ስለዚህ ምን ይላሉ ብሎ ላቀረበላቸዉ ጥያቄ፥ አይን ከማፍጠጥና ዝም ብሎ ከመቆጣት ሌላ መልስ አል ነበራቸዉም። በማከሰኞዉ ትምህርት መ/ቅዱስ ሳይሆን የሚያወሩት ሌላ ነዉ በማለት ላቀረቡት ምክንያት ለምን ይህን ቀ ደም ብሎ የተወከለዉ ኮሚቴ አላቀረበዉም። ቄስ ብርሃኑ የዚህ ኮሚቴ አባል መሆናቸዉ ይታወቃል።

ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ የአሁኑ ሰበካ ጉባኤ በመርሐ-ግብሩ ላይ የሚሳተፉትን ወጣቶች በ 21/5/2000 እ.ኢ.አ አነጋግሯቸዉ ነበር። በእለቱም የተገኙት ወጣቶች ስለተዘጋበት ጉዳይ የበለጠ እንረዳለን ብለዉ ሲጠብቁ፤ ቄስ ብርሃኑ በራሳቸዉ ፈቃድ እንደዘጉትና በእለቱ ግን ወጣቶቹ የተጠሩበት ምክንያት በቅርቡ አቡነ መልከ ጼዴቅ እንዲመጡ በሚፈረመዉ ወረቀት ላይ የእነሱ ተሳትፎ እንዳለበት ለማወቅ ነበር። እነዚያ የወቅቱ የሰበካ ጉባኤ አባላትና ቄስ ብርሃኑ ከዚህ አነጋገራቸዉ እንደምን ረዳዉ ዲሞክራሲና ነጻነት ባለበት ሀገር ላይ መኖራቸዉን የዘነጉና ሰዎችን በግል ህይወታቸዉ ሳይቀር ሊቆጣጠሩዋቸዉ እን ደሚያልሙ ነበር።

ከሁሉ በላይ የሚገርመዉ የሚያስተምሩትን ትምህርት እየሰሙ፤ በእጃቸዉ ሥጋዉንና ደሙን እየተቀበሉ የነበሩ ጥቂት ሰዎች ቄስ ብርሃኑ የነገሯቸዉን ብቻ በመስማት ፤ ባለማመዛዘን ወይም የቄስ ብርሃኑ የውስጣቸውን ደባ የማይገልጸው ሁለተኛው ፈገግታዊ አቀራረብ የማረካቸዉ ይመስላል፤ ብዙ ምእመናን እዉነቱን ከሀሰት ለመለየት ተስኖአቸዋል።

<u>ለመሆኑ ቄስ ብርሃኑ እኝህን መንፈሳዊ አባት አቡነ መልከ ጼዴቅን እንዲህ ሊጠሉአቸዉ ሊያማሩቸዉ ያበቃቸዉ ምክንያት ምንድን ነዉ?</u>

1) በመስከረም 1999 እ.አ.አ በተካሄደዉ የካህናት ጉባኤ ላይ ቄስ ብርሀኑ በማማረር «.....እኔ ከኪሴ ብዙ ብር አዉጥቼ አስተናግጃቸዉ እንዴት ለጃማይካ ቄሶች ሹመት ሲሲጡ ለእኔ ነፈጉኝ.....« በማለት ምሬታቸዉን መግለጻቸዉ የሚያሳየዉ ስሥልጣን የነበራቸዉን ከፍተኛ ጉጉት የሚያንጸባርቅና፤ ሹመቱን ደግሞ ባለማግኘታቸዉ ቂም የያዙ ለመሆናቸዉ ዉሎ አድሮ ከፈጸሙዋቸዉ ድርጊቶች ለመረዳት እንኳን ቀረብ ላለ ለራቀም ቀላል ነዉ። በመሠረቱ ነጋ ጠባ ደመወዝ አነሰኝ፣ ልጆቼ ተራቡ፣ ቤተሰቦቼ ጦም አደሩ የሚሉት እኝሁ ቄስ ከራሳቸዉ ኪስ አዉጥተዉ ይህን አደረጉላቸዉ ቢባል ማንም ሊያምን አይችልም። ያደረጉላቸዉም ካለ ከቤተክርስቲያን ለአቡነ መልከ ጼዴቅ ወጪ የተባለዉ ነዉ፤ እሱም ቢሆን ለእሳቸዉ የሹመት እጅ መንሻ ሳይሆን አቡኑ በቆይታቸው ላደረጉት መልካም ሥራ፤ ለቤት ኪራይና ለትራንስፖርት የተከፈለው ነው።

2) ሌላው፤ እኝህ አባት ከመጡ አንስቶ ተራርቀዉ የነበሩትን ካህናት እንዲቀራረቡና ወደ ቤ/ክን በመምጣት በአንድነት ምእመናኑን እንዲያገለግሉ ማድረጋቸዉ ነው። ይህ ደግሞ ቄስ ብርሃኑ የማይፈልጉትና ሌሎች የተማሩ አገልጋዮች ከመጡ ህልውናቸው አጠያያቂ የሚሆን ስለሚመስላቸው ነበር። ቄስ ብርሃኑና ጀሌዎቻቸው በይፋ የሚናገሩት ግን አቡነ መልከ ጼዴቅ በዚህች ቤተክርስቲያን አማካኝነት ለምሁር ገዳመ ኢየሱስ እርዳታ ሰበሰበዋል የሚል ነበር። መልካሙንም ነገር እንደ ወንጀል አድርገዉ በማዉራታቸዉ የራሳቸዉን ምንነት ለማረጋገጥ ችለዋል። ይህ ደግሞ ወንጀል ሆኖ ከተቆጠረ መቼስ ምን ይደረግ!! በተረፈ ሌላ ተጋኖ የሚሰማዉ አሉባልታ የአቡኑን ሥም ለማጥፋት እንጂ እዉነታዉ ከላይ የተገለጸዉ ነዉ።

3) አቡነ መልከ ጼዴቅ ከመጡ ጊዜ ጀምሮ ካህናትን በማሰባሰብ ስለ መንፈሳዊ አገልግሎት በየጊዜዉ ያወያዩ ነበር። ይሁን እንጂ ቄስ ብርሃኑ ምንም አይነት ዉይይትን ስለማይደግፉ፤ ከመሰሎቻቸዉ ጋር በመንደር መሰብሰብን ይመርጡ ነበር። የቤ/ክኗ ሰላም በእሳቸው የግል ፍላጎት ላይ እንዲመሰረት ከማሰባቸው የተነሳ የፈጸሙት በደል በዚህ አነስተኛ ጽሁፍ ስለማያልቅ በሁለተኛው ስለምናብራራው እዚህ ላይ ይቆየን።

<u>5.3 ነሐሴ 1999 እ.አ.አ ብጹእ አቡነ ኢሳይያስ፤</u> የቄስ ብርሃኑን ችግር ፈጣሪነት ቢረዱትም ታግሰው በመቆየት የአዲስ የሰ/መ/አ/ጉባኤ አባላት ምርጫ ወቅት በእንግድነት በቤ/ክናችን በእለቱ ከነበሩት ከብጹዕ አቡነ ቁርሎስ ጋር በመሆን በወቅቱ የነበረው የሕግና ሥነሥርዓት ጥያቄ ሳይፈታ፥ ሰላም ካመጣ በሚል ሽፍንፍን የብዙኃኑን ጥያቄ ወደ ጎን በማለት ምርጫ ሳይሆን የተወሰኑ ሰዎች በሰ/አ/ጉ/አባልነት ቢሰይሙም፥ ያው የሰየሙት ጉባኤ መልሶ ከእሳቸው ጋር በአሠራር ተዋረድ መግባባት ባለመቻሉ ብዙም ሳይሰሩ፣ (ሳይቆዩ) ተመልሰው ሄደዋል። የሚያዛዝን ቄስ ባለመታደሉ ነው እንጂ መዝገበ-ቅዳሴና ሰዓት ከነምልክቱ ሊያስተምሩት የሚችሉትን አባት፥ በራሱ በመምሬ ብርሃኑ ተንኮል ተመልሰው ሄዱ። በዚያ ወቅት ስለተፈጠረዉ የሰ/መ/አ/ጉባኤ አባላት አመራረጥ ዝንፈት በተመለከተ በተለይ የአስመራጭ ኮሚቴ የፈጸመዉን ስህተት ወደፊት እንዳይደገም ከአስፈለገ በጽሁፍ የሚከተሉት የአስመራጭ ኮሚቴ አባለትም ሆነ ምእመናን እንዲያዉቁት ማድረግ የሚቻል መሆኑን እናሳስባለን።

## 6.0 እንደማናችንም በስደት መጥተው የቤ/ክኗን ሰላም የሚያደፈርሱት መምሬ ብርሃኑ ብስራት አገልጋይ ወይስ ******?

መምሬ ብርሃኑ እ.አ.አ. 1993 መጨረሻ ገደማ ከኢትዮጵያ ወደ ሆላንድ ተሰደዉ ጥቂት ሳምንታት ይቆዩና ከዚያም ወደ ኢንግላንድ ምድር ያቀናሉ። ከመጡበት ጊዜ አንስቶ ሙያቸው አነስም በዛም ባላቸዉ አቅም ከቤተክርስቲያን በመገኘት ከእርሳቸው በፊትም ሆነ በኋላ እንደተሰደዱት ካህናት ከማገልገል ተቆጥበዉ አያዉቁም። ለዚህም ሊመሰገኑ ይገባል። ይሁን እንጂቄስ ብርሃኑ ብሥራት ከአቡነ ዮሐንስ እረፍት በኋላ የአምባገነንነት፣ የፍቅረ ንዋይ፣ የፍቅረ ሲመት(ሹመት) ለእኔ ብቻ የሚል ባሕርያቸዉ የበለጠ ግልጽ እየሆነ መቷዋል። የራሳቸዉንም ጥቅም ለማስጠበቅ ሲሉ ምእመናንንና ካህናትን መከፋፈልና ማለያየት የእለት-ተእለት ተቀዳሚ ሥራቸው አድርገው ተያይዘዉታል።

«የእግዚአብሔር ቃል ህያዉና የሚሰራ ነዉ፣ ሁለት አፍ ካለዉ ሰለት ይልቅ ስለታም ነዉ ነፍስንና መንፈስን ጅማትንና ቅልጥምን እስኪለያይ ድረስ የሚቆርጥ ነዉ፣ በልብ ዉስጥ የተሰወረዉንም ሃሳብና ምኞት መረምሮ የሚፈርድ ነዉ፣ ከእግዚአብሔር ፊት የሚሰወር ምንም ፍጥረት የለም በእርሱ ፊት ሁሉም ነገር ግልጥና እርቃኑን ሆኖ የሚታይ ነዉ» እኛም መልስ መስጠት የሚገባን በእረሱ ፊት ነዉ» ይላል ዕብራዉያን 4፣12-13

እንግዲህ ቄስ ብርሃኑ ብስራት የተሰወረዉን ገልጦ በሚያይ አምላክ ፊት ቆመዉ በተለምዶይቱ የማለያያ ዘዴ ካህናቱን ከሁለት ከፍለዉ ምእመናኑንም ከሁለት ከፍለዉ ግማሹ እሳቸዉን ደግፎ ካህናት አያስፈልጉንም አንድ ቄስ አንድ ዲያቆን ይበቃናል እንዲል፣ ሌላዉን ደግሞ እሳቸዉ ለመደገፍ የሚያሳዝን ነዉ እያለ ሲሄድ ከሁሉም ጉዳዩን ያልተረዳዉ ምክንያቱን

በሚገባ ለምን አታስረዱንም ጭቅጭቁ ከየት ነዉ የሚመነጨዉ እያለ ይጠይቅና ከዛሬ ነገ ይሻል ይሆናል ተመካከሩ ብሎ ጸሎቱ ሲያልቅ እየወጣ ይሄዳል። በዚህ ዓይነት ቀኗን ከሌሊት በተንኮል የሚያሳልፏት መምሬ ብርሃኑ ብስራት በ2000 ዓ ም በጥር ወር የሰበካ ጉባኤ ምርጫ ሲካሄድ መቼም ለማሳደምና፣ ለማለያየት ተወዳዳሪ የላቸዉም። የሚፈልጓቸዉን ሰዎች በሰ በካ ጉባኤ እንዲገቡ ካደረጉ በኋላ ሰብሰብ አድርገዉ በሉ ያለኋችሁ አገልጋይ እኔ ብቻ ነኝ እና ደመወዜን ከፍ አድርጋች ሁ ጣራ አስነኩልኝ ብለዉ ይማጸናሉ፣ ሁልጊዜ እንደሚሉት በረሃብ ከነቤተሰቤ ማለቁ ነዉ። መደበኛ ሆኜ የማገለግላችሁ፣ የማቆርባችሁ፣ ያጋባኋችሁ ቄስ እኔ እኮ ነኝ እያሉ ሊያግባቡ ቆይተዉ፤ በመጨረሻ በድብቅ እነ ስም አይጠሩ ከ240 ፓዉን ድ በአንድ ጊዜ 600 ፓዉንድ ያደርሱላቸውና በሉ እንዲህ ከሆነ እስከ አሁን የቤ/ክኑን ቼክ በኪስዎ ይዘዉ ገንዘቡን እንደ ፈለጉ አዉጥተዉ በሉት እየተባለ ነዉና ይህን ለመከላከል ቼኩን ሌላ ሰዉ ይያዝ፣ በባንክ ፊርማም አይግቡ እኛ እስከለን ምን ችገረዎት ይባሉና ፈራሚዎች ከጠቅላላዉ ጉባኤ የተመረጡ አባላት ይሆናሉ። አድሬ የራሳቸዉ 600 ፓዉንድ ከሞላ ለ ሌላዉ ችግር ግድ የላቸዉም። ቀጥለዉም ደግሞ ያቺ በረጅም ቀሚስና ካባ ታጅለዉ የሚኩነሰነሱባትን አስተዳዳሪነት መቋ መጥ ይይዛሉ። እሱዋን ደግሞ በግርግር አስፈጽሜ አቆናጠጣለሁ ብለዉ በጠሩት ስብሰባ ላይ ያለፈዉ የሰበካ ጉባኤ አስተ ዳደር ምርጫ ከሕግ ዉጭ ነዉ አልተሟላም እና መስተካከል አለበት ተብሎ ቄሱ ያልጠበቁት ዱብእዳ በተሰብሳቢዉ ተስ ተጋባ። የሁሉም ድምጽ አይሎ የጎደሉትን አባላት የሚያስተካክሉ ከምእመናን እና ከካህናት የተዉጣጡ 5 የአስመራጭ ኮ ሚቴ በእለቱ ተሰይሞ በቄሱ የግል ችግር ሳይስተካከል የነበረዉ የአባላት ብዛት በቃለ አዋዲዉ ሕግ ላይ ተመርኩዞ በተካሄ ደ ምርጫ እዉን ሆነ። አሁን እንግዲህ የወደፊቱ የግለሰቡ ጥያቄ ከፍተኛ ፈተና ሊገጥመዉ ነዉ። የባንኩ ፈራሚዎች የነ በሩት የሰበካ ጉባኤ አስተዳደር ም/ሊቀመንበር፣ ዋና ጸሀፊ፣ የገንዘብ ግምጃ ቤት ነበሩ። ከዚህ በፊት በጉባኤው ተወክለው በተለያየ ምክንያት መሥራት አንችልም ባሉ አባላት ምትክ በሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ምርጫ ወቅት በተጠባባቂነት ካሉት ከፍተኛ ድምጽ ያገኙት ፈቃደኝነታቸውን ጠይቆ ማምጣትና በሕጉ መሠረት እንዲተኩ ተደረገ። በዚያ መሠረት በእ ሁኑ ሰዓት ያሉት ጠንካራ የሂሳብ ባለሙያ ጭምር እንዲገቡ ተደረገ።

አባላቱ በዚህ መልክ ሲሟሉ አዲስ የሥራ ድልድል ለማድረግ ስምምነት ላይ ይደርስና በቃለ አዋዲዉ ሕግ መሠረት ም/ሊ ቀመንበር ከምእመናን ከካህንም ሊሆን ስለሚችል የድምጽ አሰጣጡ በወረቀት ሆኖ ም/ሊቀመንበር ከምእመናን፣ ዋና ጸሐፊ ከካህናት ፣ ገንዘብ ቤት ከካህናት ሆኖ በከፍተኛ ድምጽ ይመረጣል። በዚህ ጊዜ ሂሳብ ሰራተኛ ናቸዉ የተባሉት ሰዉ በዉ ጪም ከምእመናን የተመረጡ አንዲት ሴት አሉ ይባል ነበር። ተጨማሪዎች ሲገቡ የታየዉ ግን አሳፋሪ ነዉ። ቄስ ብርሃኑ ሲጠየቁ የሂሳብ ሰራተኛዋ ጊዜ ስሌላቸዉ እየተረዳዳን ነዉ ስንሰራ የቆየነዉ እኔም ፣ዶ/ር በቀለም ፣ ዲ. ደረጀም ሰርተናል ይላሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ ቄሱ በግላቸው የሂሳቡ ሥራ ውስጥ እንዲህ አደረጉ እንዳይሉ የእሳቸውን ውሸት ማጋለጥ መሆኑን ተ ረድተው ዝምታን መርጠዋል። ከዚያ በኋላ ይህ ትክክል አይደለም፤ እራሱ ተከፋይ የሆነ ሰው፣ ገንዘብ ከባንክ እየፈረመ የ ሚያወጣ ሰዉ ሂሳብን በወጪና ገቢ የመመዝገብ ሐላፊነት ዉስጥ መግባት የለበትም በማለት ያለፈው ከሕግ ውጭ የሆነው አሠራር እንዲስተካከል ጉባኤው ወሰነ።

ሥራዉ በዚህ አይነት ሲቀጥል መምሬ ብርሃኑ አዲስ ነገር ታያቸዉ ፤ እሱም የባንክ ፈራሚ መሆን ያለብኝ እኔ ነኝ በአዲ ሱ የቃለ ዓዋዲ አሠራር መሠረት እኔ አስተዳዳሪ ነኝ የሚል ነገር አመጡ። ይህ በዚህ ሀገር የበጎ አደራጎት ሕግ መሰረት አ ይሰራም፤ ገንዘብ የሚከፈለዉ ሰዉ ለራሱ ቼክ እየፈረመ መዉሰድ አይችልም ቢባል ፈጽሞ አሻፈረኝ በሌላ ሀገሮች የሚገኙ ትንም በስልክ ጠይቄአለሁ ራሳቸዉ ናቸዉ የሚፈርሙት፤ ስለዚህ እኔ መፈረም አለብኝ ሆነ። ከሰበካ ጉባኤ አስተዳደር አ ባላትም የሌሎቹ ተመረጦ መጨመር ጉዳቸዉን እንደሚያወጣዉ ስላወቁ የተወሰኑት ፈራሚ ቢሆኑ ሲሉ ከፊሎቹ ፈራሚ ሊ ሆኑ እንደማይችሉ በሚገባ ገልጸዉላቸዋል። ዉሳኔዉ አልቆ ወደተግባር ሲለወጥ እንቅፋት የሆኑት ቄስ ብርሃኑ ችግር አለ በማለት ለሰላም ኮሚቴ አቅርበዉ በነሱም በኩል የሰበካ ጉባኤ አስተዳደር ዉሳኔ ትክክል መሆኑን አረጋግጠዋል። አሁንም ነገር የማይታክታቸዉ ቄስ ብርሃኑ እንደገና መልካቸዉን ለዉጠዉ በደብዳቤ ላይ አስተዳዳሪ ብዬ መፈረም አለብኝ ሲሉ አ ዲስ ጥያቄ አመጡ። መቼ ተሾሙ? ማን ሾመዎት? ሲባል ማስረጃ ከየት ይምጣ፤ ለዚህም በቂ ምላሽ ተሰጥቶበት በሰበካ ጉባኤ አስተዳደር የበላይነት ሥራዉ እንዲካሄድ ተደረገ። የሚገርመዉ እስከዚያ ድረስ ከደመወዛቸዉ ሌላ የመኖሪያ ቤታቸ ዉ የስልክ የፋክስ ፍጆታ እየተከፈለላቸዉ ነበር። አይከፈልላቸዉ አይደለም ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ከሆነ ግን በመጠኑ ሃላፊነት ሊሰማቸዉ ይገባል እንጂ የጠላት ብር ይመስል ያለአግባብ ማዉጣት በእዉኑ እኚህን ሰዉ ለቤ/ክኗ የገንዘብ ቁጠባ ያስባሉ ለማለት አያስደፍርም። በእንጻሩ አቡነ ዮሐንስ በሕይወት በነበሩበት ዘመን ለስልክና ለፋክስ የተፈቀደላቸዉ በየ3 ወ ር60 ፓዉንድ ነበር ማለት ወደ 240 በዓመት። ይሁን እንጂ እኔም ለራሴ ጉዳይ ስለተጠቀምኩ ብለዉ በሙሉ አያስከፍሉም ነበር። የቄስ ብርሃኑ የዓመት ወጪ ግን በሂሳብ ሪፖረቱ ላይ እንደተብራራዉ በአማካኝ በዓመት ወደ 1,300 ፓዉንድ ነበር።

ካህናቱም ሆነ ቁጥራቸዉ በርከት ያሉ ምእመናን ለምንድን ነዉ ቄስ ብርሃኑን ለክህነት ብቁ አልነበሩም/አይደሉም የሚሉት?

ወደኋላ መለስ ብለን በእኚሁ ካህን ከተፈጸሙት በርካታ በደሎች መካከል ጥቂቶቹን ለማስታወስ ያህል ብናነሳ፤

## 6.1 ክህደታቸው፣ ካህናትና ምእመናንን ለመከፋፈል ከፈጸሙት፤

1. ባህታዊ ገ/መስቀል ወደ ለንደን ከ6 ዓመታት በፊት በመጡ ጊዜ እያስተማሩ ሰንብተዉ ምእመናን በመድኃኔዓለም ሥም በየሳምንቱ ቅዳሜ እየተሰባሰቡ እንዲጸልዩ ካሳሰቡ በኋላ ለዚህም ቄስ ብርሃኑ ሃላፊነቱን ሊወስዱ በአደባባይ ቃል ገብተ ዉ ነበር። ይሁን እንጂ በሳምንቱ በዚያዉ አደባባይ «.........እንዚህን ባህታዉያን ብሎ አስተማሪ.......» በማለት ሌሎች ቃላትን በማከል በአንድ ራስ ሁለት ምላስ ሆነዉ ታይተዋል።

ይህ ቃለ አባይነት በድጋሚ የዛሬ ሁለት ዓመት አካባቢ በኢትዮጵያ ተራድኦ አዳራሽ እየተሰባሰቡ ስለ ቤተክርስቲያኒቱ ህይወት የሚነጋገሩ የቤተክርስቲያኒቱ ልጆች እ.አ.አ በመጋቢት 2000 ጠርተዉ ስላለዉ ችግር የሰላምና የአንድነት መጥፋት ምክንያቱን እንዲያስረዱ ሲጠይቁአቸዉ ፤ ሽምጥጥ አድርገዉ «...በእኛ ካህናት መሀከል ምንም ልዩነት የለም ፍጹም ፍቅር ነን ........» በማለት ያለ ዕፍረት ተናግረዋል። ይህ ክህደታቸዉ የሚከተለዉን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንድናስታዉስ ያደርገናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሲያስተምር «..ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን ፤ ከዚህ የወጣ ከክፉ ነዉ» (ማቴ. 5፤37) እንዲሁም በመጽሐፈ ሲራክ ላይ «.. በትእቢት ሌላዉን በመናቅ የሚደረግ ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ መሆኑን፤ ከሁሉም ደግሞ ክህደት የከፋች ናት ይላል።» መጽ. ሲራክ 10፤ 7 ይህ ብቻ አይደለም «.. የሃሰተኛ ሰዉ ጉስቁልናዉ ጽኑ ነዉ የሰነፎች ነገራቸዉ የተጠላ ነዉ።» መጽ. ሲራክ 20፤ 24 የሚለዉን ማየት ይገባቸዉ ነበር።

2. የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ምርጫ ተብሎ ስያሜ በተካሄደበት እለት (እ.አ.አ 16. 01. 2000) እምሽቱ ላይ በብጹእ አቡነ ቄርሎስ የተመራው ስብሰባ ላይ የተነሳውን አጀንዳ በተመለከተ አንዱ ካህን አስተያየታቸውን እየሰጡ እያለ ቄስ ብርሃኑ በመሃል በማቋረጥ ሁሌም እንደሚያደርጉት እኔን ለመጉዳት ነው ብለው መሳደብ ይጀምራሉ፤ ለጊዜው ይተው ቢባሉ አሻፈረኝ በማለት መሳደባቸውን ይቀጥላሉ፤ ስብሰባው እንዳለቀ ተናጋሪውን ተከትለው ልማታ ሲሉ ሌላው ካህንም አይ እኝህ ሰው ታመው ነው ብለው ጸበል ቢጤ ይረጯቸዋል። ሚስትም አባሪ ሆነው ካልተማታሁ፣ በማለት ሲጋበዙና ያዙኝ ልቀቁኝ ሲሉ ያመሹና፤ በሌላ ቀን ለሌሎች ምእመናን ተደበደብኩ ብለው ተራ ወሬ በማዉራት በምእመናንና በሌሎች ካህናት መሀከል ልዩነት እንዲፈጠር ለማድረግና፤ ለመከፋፈል አንዱን ካንዱ ለመለያየት እንደለመዱት ሲጥሩ ታይተዋል ።

3. እ.አ.አ (በ 28.06. 2000) ማንም ሳያዉቀዉ ራሳቸዉን የቤተክርስቲያኒቱዋ አስተዳዳሪ ነኝ በማለት በበራሪ ወረቀት ላይ ስማቸዉንና አድራሻቸዉን እያተሙ በማደል በቤተክርስቲያን ሥርዓት በማፋለስ ሌሎችን ስለጉዳዩ የማያውቁትን የዋሆች እንዲሁ በማሳሳት ቤ/ክኑን ሰላም ለመንሳት ብዙ ሲደክሙ ተስተዉሏል።

4. እ.አ.አ 29. 07.2000 በቤተክርስቲያን ዉስጥ አንድ ምእመን የቤተክርስቲያኗ ወጪ ሊቆጠብ ያስፈልጋል ብለዉ አስተያየት በሰጡበት ወቅት፤ ቄስ ብርሃኑ በአደባባይ የሰጡት መልስ «ቤተክርስቲያኗ ብዙ ወጪ እንደሌለባትና ያለዉም ወጪ ቢሆን ለአባ ግርማና ለንቡረ እድ አባ ወ/ማርቆስ ለእያንዳንዳቸዉ በወር 100 እንዲሁም ለዲያቆን ተረፈ 60 ፓዉንድ ሲሆን ለሳቸዉ (ለቄስ ብርሃኑ) ደግሞ በደፈናዉ ትንሽ ለትራንስፖርት ያህል..» በማለት የሚያገኙትን ሳይገልጹ አልፈዋል። እዚህ ላይ ልንገነዘብ የሚገባዉ ዋንኛዉ የ600 ፓውንድ ተከፋይ እሳቸዉ ሆነዉ ሳሉ ፤ ራሳቸዉን በነጻ እንደሚያገለግሉ ለማስመሰል የተለመደውን የቅጥፈት ፈገግታቸውን አሳይተው አልፈዋል። ለሁሉም ይህ የተለመደ ህዝብን ለማታለል የሚያደርጉት የሞኝ ተንኮል እንደነበር መገንዘቡ የሚያዳግት አይደለም።

5. መምሬ ብርሃኑ ቂመኛ፣ ይቅርታን የማያውቁ፣ ልበቀል፣ ላሳድ፣ ላሸንፍ፣ የጠላሁትን አዋርጄ ሌላውም ይከተለኝና ይጥላው የሚሉ ሰው ናቸው። ለምሳሌ ያህል፤ ሀ) ዘወትር ሐሙስ በሚካሄደዉ መርሀ-ግብር ላይ የሚሳተፉ እናቶች፤ አባቶች፤ ወጣቶች ገንዘብ አዋጥተዉ ወደ ኢትዮጵያ ለነዳያን መርጃ ልከዉ ሳደረጉት መልካም አስተዋጽኦ፤ ከአቡነ መልከ ጼዴቅ እ.አ.አ በጥር ወር 2000 የተላከዉ የምስጋና ደብዳቤ ገንዘቡን ለላኩት ምእመናን አይነበብም ብለው ቄስ ብርሃኑ በመከልከላቸዉ በእለቱ ከፍተኛ ችግር ሊፈጠር ችሏል። ይህ የሚያሳየዉ አጋጣሚዉን ሁሉ በመጠቀም ቄስ ብርሃኑ በአቡነ መልከ ጼዴቅ ለይ ያላቸዉን ጥላቻ ለመወጣት ያደረጉት ጥረት ነበር።

6. በተደጋጋሚ በአጠቃላይ ስብሰባዎች እና በካህናት ጉባኤ ላይ የሚወሰኑት ዉሳኔዎች ተፈጻሚነት እንዳይኖራቸዉ በማድረግና ለበዓላት የሚወጡ መርሐ-ግብሮችን እንደፈለጉ መቀያየራቸዉና በርካታ የቤተክርስቲያን ምሁራን እያሉ የተሟላና የተጠናከረ አገልግሎት እንዳይሰጥ በግል ባህርያቸዉ እንቅፋት በመሆናቸዉ። ከአንድ ኮሚቴ ጋር ሌላ ቃል መግባትና ወስኖ ወደሌላው ሲሄዱ ደግሞ ያንን ቃል ቀይሮ ግጭት በመፍጠር እንደገና የመሀል ዳኛና ችግሩን ለመፍታት የሚያስቡ የሰላም ሰው መስሎ መታየት፣ የሚገርሙና እራሳቸውን በማታለል በቤ/ክን ላይና በእድሜአቸው የሚቀልዱ ሰው ናቸው። በቤ/ክርስቲያናችን ለአገልግሎት መጠናከር ንዑሳን ከሚቴዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቋቋሙ ቄስ ብርሃኑ በኮሚቴው ቁጥር ባህርያቸው በየቀኑ እየተለዋወጠ ለስራ እንቅፋት ሆነዉ ይገኛሉ። በአጭሩ መምሬ ብርሃኑ ጊዜ አልገታቸው ያለ የማይማሩ፣ ነገሮችን ከሂደታቸው ጋር በማየት ለቀና ነገር መገዛት ያቃታቸው፣ በልቼው ልሙት የሚል መርህ ያላቸው ሰው ናቸው።

7. ቤተክርስቲያኒቱ በሥርዓት ትመራ ዘንድ የዉስጥ መተዳደሪያ ደንብ እንዲወጣ ከተባለ በኋላ፤ ጥቅሜን ያስቀራል በማለት ይህ ደንብ ከፍጻሜ እንዳይደርስ በማፈን እንዲያዉም ከካህን ቀርቶ ከምእመንም በማይጠበቅ ሥነ-ምግባር ፤ እየተሳደቡ የተሰጣቸዉን የረቂቅ-ደንብ ጥራዝ ከአርቃቂው ኮሚቴው አባል ላይ ሲወረዉሩ ታይተዋል።

8. ቤተክርስቲያኒቷ የዉስጥ መተዳደሪያ ደንብ ወጥቶ በሥርአት እንዳትመራ እንቅፋት መሆናቸዉ። የቄስ ብርሃኑ አስተያየት ይህን በተመለከተ እንደወቅቱ የመለዋወጥ ባህርይ ያለዉ ከሁለት ሁኔታዎች አኳያ ነዉ። ጳጳሳትና ካህናት ከኢትዮጵያ ወደዚህ በሚላኩ ጊዜ የሕጉን መዉጣት ይደግፋሉ፤ ለምን ቢሉ በረቂቁ መተዳደሪያ ደንብ በአንቀጽ 11 ቁጥር 11.1 ላይ የቤተክርስቲያኒቷ አስተዳዳሪ በማህበረ ካህናትና ምእመናኑ የሚመረጥ መሆኑን ስለሚገልጽ በጊዜዉም በለንደን የነበሩ አገልጋይ ቄስ እሳቸዉ ስለነበሩ ዞሮ ዞሮ የቤተክርስቲያኒቷ አስተዳዳሪ እሆናለሁ በማለት ተስፋ ያደርጉ ስለነበር ነዉ።

ይህ የሆነዉ ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገ/አማኑኤል የመጡ ጊዜ ብቻ ሳይሆን አቡነ ኢሳይያስ በመጡ ጊዜ በአደባባይ የደንቡን አስፈላጊነት እስከመናገር ደረሰዉ ነበር። ነገር ግን የአቡነ ኢሳይያስ በዚች ቤተክርስቲያን የአስተዳደር ኃላፊነት የሌላቸዉ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ፤ አሁንም እኔዉ ነኝ አስተዳዳሪ የምሆነዉ በማለት የዉስጥ ደንቡን ነገር ቸል ብለዉታል ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ወደ ለንደን የመጡ ካህናትን ስም በማጥፋት ፣ እንዲሁም ጸያፍ ንግግርን በመናገርና ከምእመናን ጋር በማጣላት ከቤተክርስትያን እንዲርቁ ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል፣እያደረጉም ነዉ፤ በዚህም የተነሳ አሁንም ብቸኛ አገልጋይ ሆነዉ መኖር ይሻሉ።

በሌላ በኩል የዉስጥ መተዳደሪያ ደንቡ እንዳይጸድቅ የሚቃወሙበት ምክንያቶች፤

8.1. ካህኑ በቼኮች ላይ በመፈረም ገንዘብ ለማዉጣት ስልጣን ስለማይኖረዉ፣ በተለይ ቄስ ብርሃኑ ይህን በግልጽ ከመቃወም አልተቆጠቡም። ይህ አንቀጽ የተረቀቀበት ምክንያት በዚህ ሀገር ሕግ በቻሪቲ ደንብ መሰረት ማንኛዉም ደመወዝ ተከፋይ የሆነ የቻሪቲዉ አባል መሆን ስለማይችል እና ካህናትን ከገንዘብ ጋር ከተያያዘ አሉባልታ ለማዳን ታስቦ ነዉ። እርሳቸው ግን በየጊዜው ደሞዝ ተከፋይ፣ ቼክ ያዥና ፈራሚ በመሆን የቤ/ክኑን ገንዘብ ይናኙበት ነበር።

8.2. የቤተክርስቲያኒቷ አስተዳዳሪ የሚመረጠዉ በዚች ሀገር በቂ ካህናት (ቀሳዉስት) ካሉ እየተወዳደሩ በየሶስት ዓመት ይመረጣል የሚለዉን አንቀጽ ስለማይወዱት፤ ምክንያቱም እስከመጨረሻዉ ድረስ እሳቸዉ ብቻ የዚህ ቤተክርስቲያን ተጠሪና አዛዥ መሆንን ስለሚያልሙ። ባለመታደል እንጂ እዚህ በምንኖርበት በሰለጠነው ሀገር እያንዳንዱ ለተወሰነ ጊዜ ኃላፊነቱን ተወጥቶ ለተተኪው በሰላም የሚያስረክበውን ሂደት በዐይን እያዩ አለመማር፤ ችግሩ በደም ውስጥ ያለ አምባገነንነትንና ከውስጣቸው የመነጨ ለእኔ ብቻ የሚል የእሳቸው ችግር ነው።

8.3. የዉስጥ መተዳደሪያ ደንቡ የቤተክርስቲያንን ህልዉና በተመለከተ ማንኛዉም ዉሳኔ ጠቅላላ የሰበካ መንፈሳዊዉ ጉባኤ እንጂ የአንድ ካህን ወይም ምእመን ብቻ ሊወስን እንደማይችል ስለሚያስገነዝብ እርሳቸዉም ይህን ስለማይወዱት የሚሉት ጥቂቶቹ ናቸዉ።

9. ከረጅም ጊዜ አንስቶ ራሳቸዉን የቤተክርስቲያኒቷ አስተዳዳሪ ነኝ በማለት በመሾምና ይህንንም ምኞታቸዉን እዉን ለማድረግ ካህናትንና ምእመናንን መከፋፈላቸዉ። አሁንም ነሐሴ 3 2002 እ.አ.አ በድጋሚ ይኸዉ የተጸናወታቸዉ የሹመት በሽታ አገርሽቶባቸዉ ከዛሬ ጀምሮ አስተዳዳሪዉ እኔ ነኝ በማለት በጉባኤ ተናግረዋል። ይህ የሚያሳየዉ ቄስ ብርሃኑ እያደር የአእምሮአቸዉ ጤንነት አጠራጣሪ እየሆነ መምጣቱን ነዉ። መሠረታዊዉ ጥያቄ ግን ለመሆኑ ቄስ ብርሃኑ በየጊዜዉ የቤተክርስቲያኒቷ አስተዳዳሪ እኔ ነኝ እያሉ ችግር የሚፈጥሩት ፣የሚያሸብሩት ከየት አምጥተዉት ነዉ? ከዚህ በፊትስ የሾማቸዉ ማንነዉ??

9.1 ከአዲስ አበባ ቤተክህነት ነዉ እንዳይሉ፤ ከዚህ በፊት ሊቀ ከህናት ብርሃኑ ተሹመዉ በመጡ ጊዜ በአደባባይ አቡነ ዮሐንስ እንዳረፉ በተጠባባቂነት ከቤተክህነት የተሰጣቸዉ ሹመት የተሻረ መሆኑን በቁጥር 091/548/90 በተጻፈዉ የሊቀ ካህናት የሹመት ደብዳቤ ላይ ተገልጽዋል።

9.2 ከዚያ ወዲህ ወይም ከዚያ በፊት ነዉ እንዳይባል ደግሞ ማህበረ ካህናትና ማህበረ ምእመናኑ ተሰብስቦ አስተዳዳሪ ይሁኑ ብሎ የወሰነበት ጉባኤም እንዳልተካሄደ ይታወቃል። እንዲያዉም እኝህ ካህን ግራ የተጋቡ ምእመናንን በ2000 ዓ.ም (እ.አ.አ) ለአስተዳዳሪነት እንዲመረጡላቸዉ እንደተለመደዉ በመንደር አሳድመዉ ቢመጡም ለጠቅላላዉ መንፈሳዊ ጉባኤ አቀርበዉ ዉድቅ መሆኑ ይታወቃል።

9.3 አቡነ ኢሳይያስ ሾሙኝ እንዳይሉ ጭራሽ አቡነ ኢሳይያስ ቄስ ብርሃኑ ከሚሰሩዋቸዉ ሕገወጥ ድርጊቶች የተነሳ የቤተክርስቲያኑን ማህተምም ሆነ ህጋዊ መረጃዎችንን እንዳያንቀሳቅሱ በአደባባይ በጽሁፍ ያገዷቸዉ መሆኑ የሚታወቅ ነዉ።

9.4 አቡነ ዮሐንስ በሕይወት ሳሉ በደብዳቤ ሾመዉኛል እያሉ የሚያወሩት ቢሆን ኖሮ ፤ አቡነ ዮሐንስ ግልባጭ በወቅቱ ለነበረዉ የሰበካ መንፈሳዊዉ ጉባኤ እንዲሁም ደግሞ ለካህናት ጉባኤ ወይም ሌላዉ ቢቀር በቃል ባሳወቁ ወይም ያሳዉቁ ነበር። የሆኖ ሆኖ ይህች አቡነ ዮሐንስ ሲያርፉ ብቅ ያለች ደብዳቤ እዉነተኛነቷ ከመቼዉም ጊዜ የበለጠ አጠያያቂ ሆኗል። እንዲያዉም ይህች መምሬ ብርሃኑ አለኝ የሚሉት ደብዳቤ እስከ አሁን ላልተፈቱ አንዳንድ ጥያቄዎች መልስን ሊያስገኝ ይችላል ብለው ብዙኃኑ ያምናሉ። ስለዚህ የደብዳቤው ምንጭ በከፍተኛ ደረጃ ሊታይ ይገባል።

መምሬ ብርሃኑ እንዲህ አይነት ድፍረት ከየት እንዳመጡት ለብዙዎች እንግዳ ነዉ። ከጥንቶቹ አባቶች ህይወት ጋር ምትዉዉቅ እንደሌላቸዉ ሥራቸዉ ይመሰክራል። የጥንቶቹ እንኳን ለእንደዚህ ዓይነቱ ሹመት ራሳቸዉን ማጨት ይቅርናገና ሌሎች ሊሾሟቸዉ ሲያስቡ ካሉበት በአት ይጠፉ እንደነበር በታሪክ እናዉቃለን። በቅዱስ ወንጌልም ጌታ ያስተማረን«ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን።» ማቴ. 20፤ 27 የሚል ነው።

10. የማህበረ ካህናት ጉባኤ በቤተክርስቲያን እንዳይሰበሰብ በተደጋጋሚ የቤተክርስቲያኑን ቁልፍ ይዘዉ መጥፋታቸዉ፤ ይህንና ይህን የመሳሰሉ ችግሮችን በመፍጠር ካህናቱ እንዲበታተኑና የቤ/ክኑን እድገት ወደኋላ በመጎተት፣ እንደለመዱት የሙዳየ ምጽዋቱን ገንዘብ እየለቀሙ በብቸኝነት ለመኖር ሲጥሩ ሰንብተዋል።

## 6.2 በመንፈሳዊ አገልግሎት የፈጠሩት ችግር፤

1. ለስብከተ ወንጌል እንቅፋት መሆናቸዉ፤ ለምሳሌ ዘወትር ማክሰኞ ማታ ይካሄድ የነበረዉን አቡነ መልከ ጼዴቅ የመሠረቱትን የተምሮ ማስተማር መርሐ-ግብር የሆነ ያልሆነ ምክንያት በመስጠት በገዛ ፈቃዳቸዉ ዘግተዉታል። ይህ ደግሞ የቤተክርስቲያኒቱን ዋነኛ አላማ የሚቃረን ነዉ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሳለ ሲያስተምር «...እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ፤ በወልድ፤ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ፤ ያዘዝኳችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችሁ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸዉ...» (ማቴ. 28፤ 19-29) የሚለዉን የሚቃረን ነዉ። በተጨማሪም በቃለ አዋዲዉ የሰበካ ጉባኤ አላማ የእግዚአብሔርን ወንጌለ መንግስት ማስፋፋት ሆኖ ሳለ፤ ይህንንም ያደረጉት አቡነ መልከ ጼዴቅ የመሠረቱት ስለሆነ እሳቸዉን ያናደዱ መስሎአቸዉ ነዉ። ይህ የሚያሳየዉ ቄስ ብርሃኑ ገና እንደ ህጻን ልጅ እልህ እየተጋቡ የቤተክርስቲያኗን አገልግሎት እየጎዱ መሆናቸዉን ነዉ። በእሳቸው የግል ፍላጎት ነገሩን እያጣጣሉ፣ የተጀመረው እንዲቀር አድርገዋል። ቀደም ሲልም ቢሆን በ1992 እ.አ.እ ወደ ግሪን ፓርክ ወዳለዉ ቤተክርስቲያን ስንገባ በወቅቱ የነበረዉ የሰበካ አስተዳደር ሁልጊዜ ከሰዓት በኋላ ከ 9-12፡30 ሰዓት (ከ3-6:30PM) ቤተክርስቲያኑ በማንኛዉም ቀን መጥተዉ ጸሎት ለማድረግ ለሚፈልጉ ምእመናን ክፍት እንዲሆን መወሰኑንና ለዚህም ኃላፊነቱ ለአቶ በአደ መላኩ መስጠቱ ይታወቃል። አቶ በአደ መላኩም ለረጅም ጊዜ በሰዓቱ እየተገኙ የተጣለባቸዉን ሃላፊነት ተወጥተዋል። ታዲያ የመምሬ ብርሃኑ የስብከተ ወንጌል እንቅፋትነት ምን ይሉታል ?

2. ይህች ቤተክርስቲያን አገልግሎት የምትሰጠው ለማኝ ለሆነ ሁሉ መሆኑ እየታወቀ፤ ፕሮፌሰር አስራት ወልደኢየሱስ በእረፍት ወቅት ጸሎተ ፍትሀት እንዲደረግላቸዉ ምእመናን ጠይቀዉ ቄስ ብርሃኑ ብስራት የቤተክርስቲያኗን ቁልፍ ይዘዉ በመከልከላቸዉ ፍትሀቱ ሌላ ቦታ እንዲካሄድ ሆኗል። ቄስ ብርሃኑ ይህን ያደረጉበት ፍትሀት ካደረጉ ከቤተክህነት ጋር የሚያጣላና፤ የሚያልሙትን የአስተዳዳሪነት ሹመት የሚያደናቅፍባቸዉ መስሎ ስለታያቸዉ ነበር። በዚህም ቅር የተሰኙት ምእመናን ከቤተክርስቲያን ለመቅረት በቅተዋል። ቄስ ብርሃኑ በተደጋጋሚ የወሰዱት የግል ዉሳኔ ቤተክርስቲያናችንን እና አድነታችንን ምንኛ እየጎዳዉ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን። ለነገሩ በኢትዮጵያ ከፓትርያርኩ እስከ ሊቃነ ጳጳት በጸሎተ ፍትሃቱ ላይ መገኘታቸውን ሲሰሙ፤ እይ ይህች እልቅና ወይ ከዚህ ወይ ከላይ አልመጣች ብለው ሳያዝኑ እንደማይቀሩ ምኞታቸው ይናገራል። በምኞት የሚሆን ሁሉ ከእግዚአብሔር ስላልሆነ ህልም እየሆነባቸው ተቸግረዋል።

3. እ.አ.እ. በሐምሌ ወር 2000 በቤተክርስቲያኒቷ ዉስጥ ሥርዐተ-ተክሊል ለፈጸሙ ሙሽሮች ፤ አጃቢዎቻቸዉ የለበሱት ልብስ ካሉበት ቅዱስ ቦታ አንጻር ሲታይ በደንብ ሰዉነታቸዉን ባለመሸፈናቸዉ በእለቱ የሚሰብኩት መምህር በስብከታቸዉ መግቢያ ላይ በትምህርት መልክ ወደ ቤተክርስቲያን ስንመጣ በሥርዓቱ መልበስ አለብን ብለዉ ሲናገሩ በእለቱ የተገኙት ምእመናን እዎንታቸዉን በጭብጨባ ገልጹ። ቄስ ብርሃኑ ግን በዓይን የታየውን ለማስተባበል ከስብከቱ ፍጻሜ በኋላ «እዚህ ቤተክርስቲያን ማንም እራቁቱን አልመጣም እንግዶቼን አታስቀይሙብኝ ...» በማለት የመምህሩን ስብከት ለማስተባበል ሞክረዋል። በዚህ የተነሳ ብዙ ምእመናን ቅር ተሰኝተዋል። ይህ ለምሳሌ ያህል ተጠቀሰ እንጂ በተደጋጋሚ ከወንጌል ስብከት በኋላ መድረክ ይዘው፣ ድምጽ ማጉያውን ጨብጠው አፍራሽ ሀሳብ በማቅረብ ቄስ ብርሃኑ በአንደኝነት ደረጃ የሚገኙ ካህን ናቸዉ። ከዚህም ላይ መጽሐፍ ቅዱሱን ካለመረዳታቸዉ የተነሳ ልብሳቸዉን በወጉ ሳይለብሱ የመጡትን ሴቶች ለመደገፍ ሲሉ አዳምና ሄዋን እራቁታቸዉን ነበሩ፣ አይተፋፈሩም ነበር በማለት ፍጹም የሆነ መሃይምነታቸዉን በሌላ ጊዜ በተፈጸመ ሥርዓተ ተክሊል ላይ አረጋግጠዋል።

4. ብጹእ አቡነ ዮሐንስ በድንገት በተለዩን ጊዜ ምእመናን ሥርዐተ-ቀብሩ እንዴት እንደሚፈጸም በአቡኑ ቤት በሚመካከሩበት ወቅት ከእንግሊዚህ ብቸኛ አገልጋይ ቄስ መሆናቸዉ የተሰማቸዉ ቄስ ብርሃኑ ያለምንም ሀፍረት በአራተኛዉ ቀን፤ ቤተሰቦቼ በረሃብ አለቁ እኔም ተንገላታሁ ስለዚህ ደመወዝ ይጨመርልኝ በማለት ጠይቀዉ ነበር። ሆኖም የሰበካ ጉባኤ አባላትና አንዳንድ ሽማግሌዎች የመጠየቂያዉ ወቅት በዚያን ጊዜ እንዳልሆነ አስረድተዋቸዉ ለጊዜዉ ዝም አሉ እንጂ ማመልከቻ ላስገባ እስከማለት ደርሰዉ ነበር። አጠያያቂዉ ጉዳይ እኝህ ሰዉ እምነቱ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊዉ ባህል ራሱ አላቸዉ ወይ ነዉ።

5. በዚህ ጽሁፍ ላይም ሆነ ለምእመናን ሊገለጹ የማይቻሉ ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን በተመለከተ በተደጋጋሚ ብዙ ከባድ ስህተቶችን ሲፈጸሙ የኖሩ እና አሁንም በመፈጸም ላይ ያሉ፣ ተመክረው የማይሰሙ፣ ከዛሬ ነገ ይሻሻላሉ የማይባሉ፣ ባህር ያቸዉ ተገለባባጭ የሆኑ (ውስጣቸው ሌላ በማያውቋቸው ፊት በፈገግታ የሚቀርቡ ሌላ ባህርይ የሚያሳዩ) ሰው ናቸው።

## 6.3. በገንዘብና በሥልጣን ፍቅር የቤ/ክኗ ሰላም ማናጋታቸው፤

1. እ.አ.እ በታህሳስ ወር 1999 በተደረገዉ የካህናት ስብሰባ ላይ ምንም እንኳን በቤተክርስቲያኒቷ ላይ ምንም አይነት ሹመት ባይኖራቸዉም በድፍረት «ቤተክርስቲያኒቱ ትዘጋታለች እንጂ ማንም እኔ እያለሁ የዚህ ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ ሊሆን አይችልም» በማለት በአደባባይ በሊቀጳጳሱ ፊት ዝተዋል። የራስ ወዳድነት ቀንበር ዉስጥ አንገታቸዉ ገብቶ በየስብሰባዉ ከ6 ወራት በላይ በእሳቸዉ የአበል ክፍያ የስዕለቱን ገንዘብ ልብላ በማለት ላይ ብቻ ዉይይት እንዲደረግ በየጊዜዉ አዳዲስ ስልቶች እየቀየሱ መላዉን ካህናት እና የሰበካ አስተዳደር ጉባኤዉ መፍትሄ መስጠት ከማይችልበት አዘቅት ዉስጥ ለመዝፈቅ አጋብቻችሁ፣ አቁርቤአችሁ፣ ቄስ አኮ ነኝ፤ ኸረ ስንቱ....መጨረሻዉ ግን ከየትም ይመጣ 600 ፓዉንድ አምጡ ያለበለዚያ ቤ/ክኗ በእኔ የተነሳ እንድትከፋፈል፣እንድትበተን፣ እስከመዘጋትም እንድትደርስ አረጋታለሁ በማለት በቅርቡ በ17 ሐምሌ 2

002 እ.አ.አ አቡነ አትናቴዎስ በተገኙበት ስብሰባ ላይ በግልጽ ተናግረዋል፤ ይህም የይሁዳ መርገም አድሮባቸዉ ለበጎ ነገር እንቅፋት እየሆኑ ነዉ።

2. የቤተክርስቲያኒቷን ገንዘብ ለግላዊ ጉዳይ ማባከናቸው (ለስልክ እና ለፋክስ ፍጆታ ...ወዘተ)። ዝርዝሩንና ስለገንዘቡ መጠን የሂሳብ ሪፖርቱ ላይ ይመልከቱ።

3. ቄስ ብርሃኑ በድፍረት የቤተክርስቲያኒቷን የቻሪቲ ምዝገባ በሥማቸውና በመኖሪያ ቤት አድራሻቸው እንዲሁም የቤ/ክኗን የገንዘብ አካዉንቶች በሥማቸውና በመኖሪያ ቤት አድራሻቸው አዛዉረዉ ቆይተዉ ነበር። ነገር ግን አሁን በሥራ ላይ ያለ ው የሰ/መ/አ/ጉባኤ ከጥር ወር 2001 እ.አ.አ ጀምሮ ለቤተክርስቲያኗ የራስዋ የሆነ የመልክት ሳጥን በመከራየት ሁሉም ሥ ምና አድራሻ በቤ/ክኗ ሥር እንዲሆኑ አድርጓል።

እነዚህ ከላይ በአጭሩ ለምሳሌ ያህል ተጠቀሱ እንጂ የመምሬ ብርሃኑን በመረጃ የተደገፈ የበደል ስራቸዉን ብዙ ብዙ መዘ ርዘር በተቻለ ነበር።

ቄስ ብርሃኑ እንደ ጥሩ የሰነ አእምሮ ጠበብት ሰዉን ከእድሜዉ አኳያ ፤ ስሜቱን በመገምገም፤ በመልመልመጥ፤ የአዞ እንባ በማፍሰስ እንደ ፖለቲካ ሰዉ ደጋፊዎች ለማግኘት ይህ ነዉ የማይባል የስም ማጥፋት ዘመቻ ሲያካሂዱ ወራቶች አልፈዉ ዓመታት ከተተኩ ቆይቷል። በዚህ ቅጥፍና የተታለሉ አንዳንድ እናቶችና አባቶች ወጣቶች ጭምር ሳይቀሩ «....እኛ ቀድሶ የ ሚያቆርበን ካለ የምን ትምህርት ነዉ .....» ብለዉ እስከመናገር ደርሰዋል። ይህ ሚዚያናዊ ያልሆነ አነጋገር ከመሠረተ ክርሰ ትና የራቀ፤ አሳዛኝና አስገራሚም ነዉ። ምክንያቱም እነዚሁ ሰዎች ናቸዉ ማታም ይሁን በተገኘዉ አጋጣሚ«... ሰማችሁ? እ ገሌ እኮ ወደ ሌላ ሃያማኖት ሄደ/ች.......» እያሉ ወሬ የሚያናፈሱት። ነገር ግን መሠረታዊዉ ጥያቄ መሆን የነበረበት «ለም ን ወደዚያ ሄዱ?» ነበር። የሆኖ ሆኖ መልሱ አጭር ነዉ። ሰንት ምሁራን ያላት በለንደን የምትገኘዉ ቤተክርስቲያናችን በጎ ቿን በተገቢዉ መንገድ እንዳትጠብቅ እኝሁ ቄስ በየጊዜዉ በሚፈጥሩአቸዉ የተለያዩ ችግሮች የተነሳ ስለማይሰጥ ፤ በዚህም የተነሳ በቤተክርስቲያን ዉስጥ ፍቅርና የመግባባት መንፈስ ባለመኖሩ ነዉ። ብዙዎችም በልማድ ተመላላሽ በመሆናቸዉ ፤ የ አንድ ምእመን ከቤተክርስቲያን መቅረት ምን ያህል እንደሚያስጠይቅም የተረዱት አይመስልም። በሃይማኖት መጽናት፣ ህይ ወትን ፤ አካሄድን እንደ ጌታችን ትእዛዝ ማድረግ የሚቻለዉ መጽሐፍ ቅዱስን በደንብ ሲያዉቁ እና እምነትን በእዉቀት ሲገነቡ ብቻ ነዉ።

አንዳንድ እናቶች፣ አባቶች፣ ወጣቶች ቄስ ብርሃኑ የነገሩዋቸዉን ብቻ በመቀበል፤ ባለማመዛዘን ፤ ለምን እንዲህ ሊሉ ቻሉ? ከበስተኋላ ምን ፈልገዉ ነዉ ? ብለዉ ሳያስቡ በሥርዐት ቀርበዉ የአስተዳደር ጉባኤዉንና ካህናቱን በመጠየቅ እዉነቱን ሳያ ጣሩ ፤ የተነገራቸዉን ብቻ መልሰዉ እንደ ገደል ማሚቶ ለሌላዉ በማስተጋባታቸዉ ነገሮች እንዲባባሱ አድርገዋል። ጭራሽ አንዳንዶችማ ያልሆነዉን ሁሉ እንደሆነ በማስመሰል ነገሮችን የበለጠ እንዲቀጣጠሉ መሳሪያ ሆነዉ በማያዉቁት በጥላቻና በቂም ተዘፍቀዉ ሲመላለሱ ሲታይ ያሳዝናል። ስለዚህ ግለሰብን ሳይሆን አምላካችንና ቤተክርስቲያናችንን በማስቀደም በንስ ሐ ልንመለስ ያስፈልጋል።

ቄስ ብርሃኑ አላማቸዉም ሆነ ፍላጎታቸዉ «እኔ ብቻ» ለእኔ ብቻ! ለሌላው አትጨነቁ! የሚል መመሪያ አንግበዉ ነዉ። ይህ ንንም ለማስጠበቅ ምንም ነገር ለማድረግ የማይመለሱ፤ እንደ ምድራዊ መሪዎችም በኃሳብ የሚለዩዋቸዉንም በሌሎች ሰዎች በማስጠላትና ከቤተክርስቲያን አካባቢ እንዲርቁላቸዉ እንቅልፍ አጥተዉ ያላሰለሰ ጥረት ነጋ ጠባ የሚያደርጉ ናቸዉ። እዚ ህ ቤተክርስቲያን አካባቢ ሁሉን ነገር የሚያዩት ከራሳቸዉ የግል ጥቅም አንጻር እንጂ ለዚች ቤተክርስቲያን ሆነ ለምእመናኑ ምንም ግድ የሌላቸዉ ራስ ወዳድ ናቸዉ። የራሳቸዉንም ጥቅም ለማስጠበቅ ግን ቄስ ብርሃኑ በአንድ በኩል የፓትርያርኩን አመራር ለሚቃወሙት ሁሉ እኔ ከእናንተ ጋር በመሆኔ ትልቅ ችግር እየደረሰብኝ ነዉ፣ ስለዚህ ከሲኖዶስ ጋር መሆን እያስ ፈልገንም እያሉ በሌላ በኩል ደግሞ ስልጣን ለማግኘት ከቶ ተስፋ ስላልቆረጡ በአለፈዉ የካቲት ወር 2002 እ.አ.አ ለቅዱስ ፓትርያርኩ በኢትዮጵያ ኤምባሲ በተደረገዉ የእራት ግብዣ ላይ እጅ ለመንሳት እና ምልጃ ለማቅረብ በመገኘት የመጀመሪ ያዉ ሰዉ ነበሩ። በቅርቡ ለአክሱም ሐዉልት መመለስ በተደረገዉ ስላማዊ ሰልፍ ላይ በተገኙበት ጊዜ ለአንድ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሠራተኛ፤ ይኸዉ ከእናንተ ጋር ተባብሬ ታቦቱ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ በማድረጌ ደመወዜ ተይዟል በማለት ያ ልተደረገና የማይገናኘዉን ጉዳይ አያይዘዉ ብሶታቸዉን ገልጸዋል። ይህንንም ሊሉ የቻሉበት ምክንያት በኤምባሲዉ በኩል ተሳልፎ ሹመት ከፓትርያርኩ ዘንድ አገኝ ይሆናል በማለት ነዉ።

እንግዲህ ራሱን ብቻ የሚወድና የራሱን ጥቅም ከዚች ቤተክርስቲያን በፊት የሚያስቀድም ለዚህ አገልግሎት እንደማይገባ ጌታችን ራሱ በምድር ላይ ሲያስተምር ተናግሮታል.. «መስቀሉን የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባዉም.... » ማቴ. 10፤ 37-39። የቄስ ብርሃኑ ምግባራቸዉ ሆነ ባህርያቸዉ ከዚህ ቃል ጋር የሚቃረንና ፤ለዚህ ሀዋርያዊ ተልእኮ ሆነ የቤተክርስቲያን አገልግሎት እንዳይከሄድ እንቅፋት ሆነዋል። እዚህ ላይ፤ ምናልባት መስቀሉን ይዘዉ የለም ወይ? የሚል ይ ኖራል፤ አዎ መስቀል እያሳለሙ ተንኮል መዝራትና ሳንቲም መልቀም አይደለም። ይህ ከአሁኑ አባባል ጋር ይለያያል፤ ራስን ለክርስቶስ መስጠት፣ ከሁሉ ጋር በፍቅር መኖር፣ ከገንዘብ ፍቅር (ያዉም ከስዕለት ገንዘብ) እና ከሥልጣን ፍቅር የራቁና ራ ሳቸዉን ዝቅ በማድረግ ሁሉም የሱና ከሱ የተገኘ መሆኑን ተረድቶ ለማስረዳት ቅድሚያ መስጠት ነበረባቸዉ።

«ከመጠምጠም ትምህርት ይቅደም» እንደሚባለዉ መምሬ ብርሃኑ ከትምህርት ደረጃ እዉቀታቸዉ ጋር ፈጽሞ የማይቀራረበ ዉን ስልጣንና ሹመት በመመኘት አምስት አመት ሙሉ ችግር ከመፍጠር ይልቅ በቤ/ክኗ ካሉት መምህራን ቁጭ ብለዉ ቢ

ማሩ ኖሮ እርሳቸዉ ሳይፈልጉት ሹመቱ ራሱ ፈልጎ ይመጣላቸዉ ነበር። ቄስ ብርሃኑ የመሠረተ ሃይማኖት እዉቀት እንደሌላቸዉ እራሳቸዉ የተናገሩትን ፣የጻፉትን በምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ከዚህ በፊት በየካቲት ወር 12 ቀን1992 በጻፉት ደብዳቤ ላይ ጥቅሱ «ንቁም በበህላዌነ እስከንረክቦ ለአምላክነ (ፈጣሪያችን ስለጠፋብን እስከምናኘዉ ድረስ በያለንበት እንቁም) የሚል ነበር። ማን እንደተናገረዉና ለምን እንደተነገረ ሳይረዱ፣ ንባቡን ብቻ እንጂ ምስጢሩን አላወቁትም። ታዲያ እንደዚህ ያለ ፈጣሪዉ የጠፋበት እና የት እንዳለ የማያዉቅ ካህን እንዴት የደ/ጽ/ቅ/ማርያም አገልጋይ (አስተዳዳሪ) እሆናለዉ ብለዉ ይመኛሉ። እንዲሁም በአለፈዉ የስቅለት ዕለት (ግንቦት 03/2002 እ.አ.አ) በቤተ ክርስቲያን ዉስጥ ስለ ጾም መግደፊያ የፋሲካ እለት የምግብ ዝግጅት ከሰ/መ/አ/ጉባኤው የተነገረው ማስታወቂያ ላይ ለማብራራት ሲሞክሩ ነገረ መለኮትን ካለመረዳታቸዉ የተነሳ«ምግብ መለኮት ነውና ሁላችሁም ይዛችሁ ኑ» በማለት መለኮት ምግብ እንደሚበላ አድርገው የተናገሩ ካህን በእዉቀት ላይየተመሰረተችዉን ቤተክርስቲያን በመሃይምነት እመራታለሁ ብሎ ከማሰብ አሁንም ከመጠምጠም ትምህርታቸዉን ቢያስቀድሙ የተሻለ ነዉ እንላለን።

ይሁን እንጂ ጥቂት ጀሌዎቻቸዉ እኝህ ከላይ የተዘረዘሩትን ጥፋት የፈጸሙ ቄስ አሁንም ብቸኛ የቤተክርስቲያናችን አገልጋይ ይሁኑልን፣ ይህችን ቤተክርስቲያን ይምሩ ብለዉ እምቢልታ ሲነፉላቸዉ ስናይ የብዙዎችን የመንፈሳዊ እዉቀት ብስለት ብቻ ሳይሆን የአእምሮ ጤንነትና የማመዛዘን ችሎታም ጭምር ምን ያህል እንደሆነ እንድንታዘብ አድረጎናል። የቄስ ብርሃኑ መሰሪ ባህርይ ለዚች ቤተክርስቲያን እድገትና ዘላቂ ሰላም ማጣት ዋናዉ እንቅፋት መሆኑ አሌ የማይባል ነዉ። ሰዉ 1/2/3 ጊዜ ይሳሳታል ነገር ግን በየቀኑ ለሚሳሳት፤ በጉባኤም ቢነገረዉ ለማይሰማ ፣ በሌሎች ላይ ንቀትን ለሚያሳይ፤ ለሰዎች መንፈሳዊም ሆነ ስጋዊ ህይወት እንቅፋት የሆነን ግን አሁንም እሰየዉ ቀጥልበት ማለት በቦታዉና በሀገሩ ሰዉ እንደሌለ ያሰኛል ። የዚህችን ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ የሚሾመዉ ቄስ ብርሃኑ ራሳቸዉን እንደሾሙት ሳይሆን፤ ወይም ጥቂት በመንደር የሚደግፉአቸዉ ሰዎች እሰየዉ ብለዉላቸዉ ሳይሆን የቤተክርስቲያኑዋ ሕግ በሚፈቅደዉ መሠረት ብቻ ሲሆን ነዉ። አለበለዚያ ግን መንፈሳዊነትም ሆነ ህጋዊነት አይኖረዉም። እንደዚህ ያለዉን ዉሳኔ የማህበረ ካህናትና ማህበረ ምእመናኑ ጠቅላላ ጉባኤ አትኩሮት ሰጥቶ ሊወያይበት፣ ድምጽ ሊሰጥበትና ሊያጸድቀዉ ይገባል። ካህናትና ምእመናንም ይህን መብታቸዉን የማስጠበቅ የዉዴታ ግዴታ ይጠበቅባቸዋል።

አንዳንዶች የዋሆች እንደሚሉት አቡነ ዮሐንስ ያወረሱን ቄስ ብርሃኑን ነዉ ፤ ስለዚህ ሌላ ሰዉ አናዉቅም አንቀበልም በማለት ሲናገሩ እንሰማለን። በመሠረቱ አቡነ ዮሐንስም ቢሆን እንደሌሎች ካህናት እኩል እንዲያገለግሉ አደረጉአቸዉ እንጂ ምንም አይነት ሹመት በቤተክርስቲያኗ ላይ አልሰጡዋቸዉም። ኑዛዜ ነዉ እንዳይባል አቡነ ዮሃንስ በድንገት ነዉ ያረፉት፤ በእርግጥ ሞተው አገኘኋቸው ያሉን እኝሁ ቄስ ብርሃኑና እነ ስመአይጠሬ ናቸው። እንግዲህ ኑዛዜ ህይወታቸው ከማለፏ በፊት ተቀብለው እንደሆነ አልታወቀም፤ ስለ አሟሟታቸውም የሚያጣራ ስለጠፋ ነው እንጂ በተፈጥሮ ህመም አለመሆኑ ህኪሞቹ ገልጸዋል። ሰዉ ደግሞ ቁሳቁስ አይደለም የሚወረሰዉ። ወይም ደግሞ አስተዳዳሪዉ የሚሾመዉ እንደ ቀደምት ነገስታት አባቶቻችን በዘር ሀረግ ፤በወገን ሳይሆን ለዚህ ቦታ የሚስማማዉን አስተዳዳሪ የመምረጥ መብት የቤተክርስቲያኒቷ ካህናትና ምእመናን ነዉ እንጂ በጉልበት እስቲ የምታደርጉትን አያለሁ ብለዉ ቄስ ብርሃኑ እንዳደረጉት አይደለም ለማለት ነው። በቤተክርስቲያን ታሪክ ራሱን የሾመ ሣጥናኤል ብቻ ነዉ። በኋላም ክብሩን አጥቷል። ዛሬም ዓለም በስህተት የሚነዳዉ በሱ ምክንያት እንደሆነ መምሬ ብርሃኑ ሳይሰሙ እንዳልቀሩ እንገምታለን።ነገር ግን ካህናትን፣ምዕመናንን ለማስተዳደር ከተቻለ በቂ የቤ/ክ ትምህርት ፤ ካልሆነ ደግሞ ግብረ ገብ፣ ከፍቅረ ንዋይና ከፍቅረ ሲመት ፈጽሞ መለየት ያስፈልጋል። በቄስ ብርሃኑ ያደረዉ ግን የሹመቱም፣ የገንዘቡም ፍቅር ስለሆነ አጥብቀዉ በመጸለይ ከዚህ ለመገላገል እንዲችሉ እናሳስባቸዋለን ሁላችንም ልንጸልይላቸዉ ይገባል።

ተዉ አንተ ብርሃን ተመለስ ተመከር
የስዕለቱን ገንዘብ ለኔ ማለት ይቅር
ምክራችንን ስማ ጠንክረህም ተማር፤

ብርሃኑም ጨለመ ተንኮሉም በቀለ
እንዲያዉ ለብቻዬ ድርሻዬን አንስቼ ብሯን ልላፍ አለ፤

እንዲህ ያለ ትዉፊት ሳናይም ሳንሰማ
ዳግማዊ ይሁዳ አንተዉ ከሆንክማ
በስምህ ብርሃን በግብርህ ጨለማ
ጥርስህን እያየ ጉድህን ያልሰማ
ተንድፏል በብዕር ሕዝቡም እንዲሰማ፤

## 7.0 አጠያያቂ የገንዘብ ወጪዎች ከ1997-1999 እ.አ.አ

በለንደን ደ/ጽ/ቅ/ማ/ ቤ/ክ የገንዘብ አያያዝን በተመለከተ ሰፋ ያለ ዘገባ ማቅረብ በተቻለ ነበር፤ ነገር ግን ከዚህ ቀጥሎ አጠር ባለ ሁኔታ ለመመልከት የምንፈልገዉ በጣም አጠያያቂ የሆኑ ወጪዎችን ከ 1997-99 እ.አ.አ. ያለዉን ነዉ። ይህ አጠያያቂ የወጪ ዝርዝር የተወሰደዉ በጥር ወር 2000 እ.አ.አ. ሥራዉን በጨረሰዉ የሰበካ አስተዳዳር ጉባኤ ለቻሪቲ ኮሚሽን ከላከዉ የሂሳብ ሪፖርት ላይ ነዉ። ከዚህ ቀጥሎ ያለዉ ዝርዝር የሚመለከተዉም በባንክ የገባዉንና የወጣዉን ገንዘብ ነዉ እ

ንጂ ካርኒ ሳይቆረጥለት፣ ባንክ ከመግባቱ በፊት እንደ ሰንበቴ ቆሎ በከረጢት ከቄሱ እጅ የገባዉን አይጨምርም። ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የዓመታዊ ሂሳብ ሪፖርት የቤ/ክኗ ምእመናን ከቻሪቲ ኮሚሽን ማግኘት እንደምትችሉ ልንገልጽ እንወዳለን።

| የክፍያ አይነቶች | 1997 እ.አ.አ.(በፓዉንድ) | 1998 እ.አ.አ.(በፓዉንድ) | 1999 እ.አ.አ.(በፓዉንድ) |
|---|---|---|---|
| ለሠራተኛ የተከፈለ | 8,640.00 | 7,080.00 | 9,290.00 |
| ለጋዝ፣መብራትና ዉሃ | 1,265.00 | 1098.00 | 1,537.00 |
| ለመጽሀፍ ግዢና ህትመት | 332.00 | 1,324.00 | 3,265.00 |
| ለስልክና ፋክስ | 908.00 | 1,304.00 | 1,404.00 |
| ለጥቃቅን ወጪዎች | 1,624.00 | 894.00 | 1,103.00 |
| ለታክሲ | ——— | 242.00 | 50.00 |
| ለሕግ አማካሪ | ——— | 2,395.00 | ——— |
| ለብድር ክፍያ | ——— | ——— | 983.00 |
| ለዉስጥ እድሳት ተለጣፊዎች | 1,636.00 | 635.00 | 769.00 |
| ጠቅላላ አጠያያቂ ወጭዎች | 16,800.00 | 12,595.00 | 18,401.00 |

**<u>በ3 ዓመት ብቻ ጠቅላላ በአጠያያቂ ሁኔታ የባከነ ገንዘብ 47, 796.00 ፓዉንድ</u>**

**<u>ዝርዝር ዘገባ</u>**

<u>ሀ. ለሰራተኛ የተከፈለ (8336 ፓዉንድ አማካኝ በዓመት)</u>
ሁላችን እስከምናዉቀዉ ድረስ በቤተክርስቲያኑ ቋሚ ተቀጣሪ የለም። ከ1997-99፤ የትንስፖርት መጠነኛ ክፍያ ለቄስ ብርሃኑና ለጥቂት ዲያቆናት እንደሚወጣ ነዉ። የወጪዉ ብዛት ለአባላት እንተዋለን።

<u>ለ. ለጋዝ፣ መብራትና ዉሃ (1300 ፓዉንድ አማካኝ በዓመት)</u>
ቤተክርስቲያኑ የሚከፈተዉ በሳምንት ሁለት ጊዜና ለአንዳንድ ወረሃዊ በዓላትን ለተወሰኑ ሰዓታት፤ ታዲያ ይህን ያህል ወጪ እንዴት?

<u>ሐ. ለመጽሐፍ ግዢና ህትመት (1640 ፓዉንድ አማካኝ በዓመት)</u>
አንድ ሁለት ጊዜ ከተባዛዉ የተሰጥኦ መቀበያ መጽሐፍ በስተቀር ሁላችን እስከምናዉቀዉ ድረስ የታተሙም ሆነ አዲስ የተደረሱ መጻሕፍት የሉም። በተለይ የ1998 እና 1999 ወጪዎች በጣም የሚያጠያይቁ ናቸዉ።

<u>መ. ለስልክና ፋክስ (1205 ፓዉንድ አማካኝ በዓመት)</u>
በቤተክርስቲያን ዉስጥ የነበረዉ አንድ የክፍያ ስልክ ነበር.። ይህ የሚያስደነግጥ የስልክ ወጪ በዉኑ እንዴት ወጣ? ወይስ...?

<u>ሠ. ለጥቃቅን ወጪዎች (1207 ፓዉንድ አማካኝ በዓመት)</u>
እንደስማቸዉ መጠናቸዉ ባነሰ፤ ለሻማና ለጧፍ ይሆን? ከሆነማ በሀገራችን በአንድ ክፍለ ሀገር ያሉ አብያተ ክርስቲያናትን መገልገያ በሸፈነ ነበር።

<u>ረ. ለታክሲ(146 ፓዉንድ አማካኝ በዓመት)</u>
የትራንስፖርት ተብሎ ከተመደበዉ አበል ሌላ ካስፈለገ መቼም ይሁን። ግን ማብራሪያ ቢሰጥበት መልካም ነበር።

<u>ሰ. ለህግ አማካሪ (2395 ፓዉንድ)</u>
ካህናትም ሆኑ ምእመናን አዉቀዉት ለሕግ አዋቂ የተከፈለ የለም። ለየትኛዉስ ችግር ይሆን? ተከፋዩ ጠበቃስ ማን ይሆን?

<u>ሸ. ለብድር ክፍያ</u>
ይህች ወደ አንድ ሺህ ብር የምትጠጋ ክፍያ በ1999 እ.አ.አ የወጣች ሲሆን፣ ከየት ወዴት እንደተጓዘች ባለማወቃችን ሁላችሁ እንድትታዘቧት ብለን ነዉ ያወጣናት። አበዳሪዉ ፣ ተበዳሪዉ፣ ተመላሽ ወይስ በወጭ ተመዝግባ የቀረች?

<u>ቀ. ለዉስጥ እድሳትና ተለጣፊዎች (1013 ፓዉንድ አማካኝ በዓመት)</u>

ሁላችን እንደምናዉቀዉ ቤተክርስቲያኑ የኪራይ ነዉ። የእድሳት ሥራ በእኛ ተደርጎ አያዉቅም። በ1992 እ.አ.አ የግሪን ፓር ኩን ቤተክርስቲያን አጽድተን ስንገባም ይህን ያህል ወጪ አልነበረብንም። ታዲያ ይህን ያህል ወጪ እንዴት ብሎ ይሆን የ ወጣዉ?

በሰኔ 16, 2002 (እ.አ.አ) በተጠራዉ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ በሂሳብ ሹሙ እንደተገለጸልን፤ በአሁኑ ጊዜ በሥራ ላይ የሰበ ካ መንፈሳዊ ጉባኤ በ01/01/2000 ከቀድሞዉ የሰበካ ጉባኤ የተረከበዉ ገንዘብ 117,074 ፓዉንድ ሲሆን ከሁለት ዓመት በአ ነሰ ጊዜ ዉስጥ የዚህ እጥፍ ከ100,000 ብር በላይ ተሰብስቦ በግንቦት 5 በባንክ የሚገኘዉ የቤተክርስቲያኗ ገንዘብ 218,500 ፓዉንድ ነበር። ቤ/ክኒቷ በ25 ዓመት እድሜዋ ያልሰበሰበችውን ገንዘብ ከሁለት ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ መሰብሰብ መቻሉ የሚያሳየው ገንዘቡ ለዘመናት በአግባቡ አለመያዙን ነው። በአሁኑ ወቅት ያለው የሂሳብ አሠራርና ሠራተኞቹ እንዲህ ዓይነቱ ን የሂሳብ አሠራር መሠረት በመጣላቸው ሊመሰገኑና እንዲበረቱበት የሁላችን ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል።

## 8.0 ቤተክርስቲያን ከዚህ ወዴት?

በአለፉት ገጾች እንደተመለከትነዉ ይህች ቤተክርስቲያን ከተመሰረተችበት ጊዜ አንስቶ ከችግር ያልወጣችና በየጊዜዉ በሚነ ሳዉ አለመግባበት ደግሞ ብዙ ምእመናን ከቤተክርስቲያኒቱ አካባቢ እንዲርቁ ሆኗል። ይህን ተደጋጋሚ ችግር ለአንዴና ለ መጨረሻ ጊዜ ለመፍታት ጥናት ያልተደረገበትና ፤ ነገር ግን ችግር ሲፈጠር ብቻ እየተሰበሰቡ ጊዜያዊ መፍትሄ መፈለግ የ ተለመደ ተግባር ሆኗል። በእርግጥ ይህንኑ በማሰብ ከዚህ ቀደም ቤተክርስቲያኒቷ በሥርዓት እንድትመራ የዉስጥ መመሪያ ይዘጋጅ ተብሎ ታርሞ ለህዝብ ቀርቦ እንዲጸድቅ በቀጠሮ ላይ እንዳለ ቄስ ብርሃኑ ችግር ስለፈጠሩ እስከ አሁን ዘግይቷል። ባለፉት 2 ዓመታት ሰኞ ማታ በኢትዮጵያ ተራድኦ ማህበር አዳራሽ ከዚያም በቤተክርስቲያን በርከት ያሉ የቤተክርስቲያኒቷ እምነት ተከታይ ምእመናን ችግሮች በዉይይት ለመፍታት ያደርጉት የነበረውና እያደረጉ ያለዉ ዉይይት ለዚሁ አላማ በመ ሆኑ ሊመሰገኑ ይገባል። አሁንም ከአለፍንባቸዉ ችግሮችና፤ ከፊታችን የተደቀኑብንን በማሰብ ፤ ያለይሉኝታ ቀጥተኛ ለሆነዉ አላማ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አማራጭ መፈለግ ይኖርብናል። ከላይ ባጭሩ ዋና ዋና ችግሮችን ለመዘርዘር የተሞከረ ሲ ሆን ከዚህ ቀጥሎ መፍትሄ ሃሳቦችን ጠቅለል ባለ መልኩ እንመለከታለን።

1) የቤተክርስቲያኗ አስተዳደሪ እኔ ነኝ እያሉ በፍቅረ ሲመት እና በፍቅረ ንዋይ ጥላ ስር ሲዳክሩ የሚታዩት ቄስ ብርሃኑ ካ ላቸዉ ራስ ወዳድነት ለዚህ ቦታ የማይመጥኑ ከመሆናቸዉ በላይ የሰዉ ምክር የማይሰሙና ለሥራ የማይመቹ በመሆናቸዉ እዚህ ቤተክርስቲያን ዉስጥ ለተፈጠሩ ብዙ ችግሮች ከሳቸዉ የበለጠ የሚጠየቅ የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። እሳቸዉ ም ደግሞ የሚመሩት በሕግ፣ በመመካከርና አብሮ በመስራት ሳይሆን ከሳቸዉ አእምሮ በምትፈልቀዉ ትንሽዬ አስተሳሰብ በ መሆኑ (በክፋትና በተንኮል ግን ተወዳዳሪ ስለሌላቸዉ) ችግሩ እየተባባሰ ነዉ። ወደ በለጠ ችግር እንዳንገባ፣ ቤተክርስቲያኒቷ በሥርዐት እንድትመራ ቃለ አዋዲዉ በሚፈቅደዉ መሠረት በተጨማሪ እንደ ሀገሩ ልማድ ሊሠራበት የሚያስችል የዉስጥ መተዳደሪያ ደንብ እንዲዘጋጅ ብዙ ምእመናን ያምኑበት ስለሆነ ፤ እስከ አሁን በዚህ ሀገር ተመዝግበንበት የምንተዳደርበት የቻሪቲ ህግ ለይስሙላ ያህል እንጂ የማንጠቀምበት በመሆኑ አዲስ የሚዘጋጀዉ ሕግ ሁሉንም እንዲያጠቃልል እና ሕጋዊነት እንዲኖረዉ ማድረግ ያስፈልጋል። ስለዚህ ይህ የዉስጥ መተዳደሪያ ደንብ በአስቸኳይ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ መደረግ ይኖር በታል። ስለዚህም እያረቀቀ ላላዉ ኮሚቴ ይህን የዉስጥ ደንብ ከፍጻሜ እንዲያደርስ እያንዳንዱ ምእመን ድጋፍ ሊሰጥ ይገ ባዋል።

2) የሰ/መ/አ/ጉባኤዉም ከማናቸዉም ሥራዎቹ ባላነሰ ትኩረት ሰጥቶ ቅድሚያ ሊሰጠዉ የሚገባ በማህበረ ምእመናን ፤ በካ ህናቱ ፤ በአጠቃላይ በቤተክርስቲያኗ ዉስጥ ያለዉን አለመግባበት አስወግዶ ፍቅር የሚሰፍንበትን መንገድ መሻት አለበት ም ክንያቱም ፍቅር ለሁሉ መሠረት ነዉና። ፍቅር ሳይኖር ሌላ ሥራ ለመስራት መሮጥ ለረጅም ጊዜ የሥራ እቅድ ብቻ ሳይሆን የዕለት ተእለት ተግባሩን ለማከናወን እንኳን አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። በተለይ ደግሞ ካህናቱ በሕብረት ሆነዉ ዘወትርም ሆ ነ በዕለተ ሰንበት ቤተክርስቲያኗን የሚያገለግሉበት መንገድ መፈለግ ለቤተክርስቲያኗ አንድነትና እምነት ጽናትና የተከታይ አ ባላቶቿን ቁጥር የሚያሳድግ እንደሆነ ጥርጥር የለዉም። ይህም ሊሆን የሚችለዉ ቄስ ብርሃኑ ለሚሰጣቸዉ መመሪያና ለሕግ ተገዢ ሲሆኑና ከሌሎች አገልጋይ ካህናትና ምዕመናን ጋር በፍቅር ሆነዉ ግልጋሎትን ሲፈጽሙ ብቻ ነዉ።

3) የሰ/መ/አ/ጉባኤ ለቤተክርስቲያኗ እምነት ተከታዮች መብዛት ፤ ወደፊት ደግሞ የሚተኩት ወጣቶች መ/ቅዱስን በበለጠ ሁኔታ ተምረዉ ማስተማር እንዲችሉ የሰንበት ት/ቤቱ የሚጠናከርበትን በአጠቃላይ የእግዚአብሔር ወንጌል መንግሥት የሚስ ፋፋበትን በመንደፍ በሥራ ላይ ማዋል ይኖርበታል። ከዚህ በፊትም በቄስ ብርሃኑ ተዘግቶ ያለዉም የተምሮ ማስተማር መር ሐ-ግብር በተዋቀረ መልኩ የሚካሄድበትን ከሰንበት ት/ቤቱ የአመራር ክፍል ጋር በመሆን መስራት ይኖርባቸዋል። በዚህ አጋ ጣሚ መጥቀስ የሚያስፈልገዉ ፤ አላግባብ ይህን የተምሮ ማስተማር መርሀ-ግብር ቄስ ብርሃኑ ሲዘጉት በመርሐ-ግብሩ ተካፋ ይ የሆኑት ወጣቶችም ለምን ተዘጋብን ብለዉ አቤቱታ ሲያቀርቡ በወቅቱ የነበረዉ የሰበካዉ አስተዳደር ጉባኤም መፍትሄ አ ለመስጠቱና ለተፈጠረዉ ችግር ከመጠየቅ እንደማይድን ሊገንዘብ ይገባዋል። ምክንያቱም በዚች በቤተክርስቲያን ዉስጥ ለ ሚወሰኑ ዉሳኔዎች የሰበካ ጉባኤዉን ብዙኋን ድምጽ የሚያስፈልገዉ ሲሆን መንፈሳዊ በሆነ ጉዳይ ላይ ደግሞ የካህናት ጉባ ኤን ምክር ሊጠይቅ ይገባዋል።

4)በማንኛዉም ወቅት የሚመረጠዉ የሰ/መ/አ/ጉባኤ ተመራጭነቱ ወይም አገልጋይነቱ ለቤተክርስቲያኒቷ ጠቅላላ ካህናትና ምእመናን እስከሆነ ድረስ የቤተክርስቲያኗን ህልዉና በተመለከተ ለሚነሱት ዓበይት ችግሮች ከካህናትና ከምእመናን ጋር በ

መሆን መፍትሄ ኃሳብ መፈለግ ይኖርበታል እንጂ ራሱን የበላይ በማድረግ አምባገነናዊ መንፈስ ሊያሳይ የማይገባዉ መሆኑን
ሊረዳዉ ይገባል። ብዙኃኑም በኮሚቴዉ አሠራር ላይ መሠረታዊ ፤ ተጨባጭ ተቃዉሞ ካላቸዉ ከሥልጣን እንዲወገድ ከወ
ሰኑ ሥልጣኑን የማስረከብ ግዴታ ይኖርበታል። በተጨማሪም ምእመናን ጥያቄ ካላቸዉ ፣ ስለ ቤተክርስቲያኗ አመራር በግል
ጽነት መነጋገር ይችሉ ዘንድ የዉይይት ጊዜ በወር አንድ ጊዜ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ሊያዘጋጁ ይገባል። ይህም አሁንበ
መምሬ ብርሃኑ የተፈጠረዉን ካህናትና ምእመናን የማለያየት እኩይ ተግባር ያስወግዳል፤ ሁሉም የራሱን የሥራ ኋላፊነት ያ
ዉቃል። መብቱና ግዴታዉንም እንዲወጣ ይረዳል።

5) ቄስ ብርሃኑ ራሳቸዉን በጉልበት የመሾማቸዉን ዜና ለጊዜዉ ተወት እናድርገዉና ፤ ሌላዉ ከፍ ያለ ችግር ለአስተዳደር
ም ሆን ለካህናቱ ያልተመቸዉ በእንጥልጥል ላይ ያለዉ የዚች ቤተክርስቲያን አስተዳደሪ ማን መሆኑ በግልጽ አለመታወቁ ነ
ዉ። ይህ በአስቸኳይ ዉሳኔ ሊሰጥበት የሚገባዉ ሲሆን ይህም የሚወሰነዉ ደንቡ በሚፈቅደዉና የአጠቃላይ ማህበረ ካህናት
ና ምእመናን ጉባኤ ሲያጸድቀዉ ብቻ ነዉ። በዚህም መሠረት ለአስተዳደሪነት የሚመረጠዉ ካህን ፤ በምግባሩ የተመሰከረለ
ት ፤ ካህናትንና ምእመናንን በፍቅር ሊመለከታቸዉ ከገንዘብና ከሥልጣን ፍቅር የራቀ፤ ሊመራቸዉ የሚችል መሆን ይገባዋ
ል እንጂ ፤ ከዚህ በፊት ቀደም ብሎ አገልግሎት የጀመረ ቄስ ብቻ ይቀጥል ማለት አይገባም። በአሁኑ ወቅት ያለዉም የአ
ርቃቂ ኮሚቴ በየተወሰነ ዓመት (እንደ ሰበካዉ ጉባኤ) የአስተዳዳሪ ስልጣን ከአንዱ ወደ ሌላዉ የሚዘዋወርበትን ሕግን እን
ዲያጤነዉ እናሳስባለን።

6) የሰ/መ/አ/ጉባኤ በቃለ አዋዲዉ የተጠቀሱትን ንዑሳን ኮሚቴዎች እንደ አስፈላጊነቱ ማዋቀር ይኖርበታል። ይህም ከሆነ
ብዙዎችን ካህናትንና ምእመናን ለቤተክርስቲያኒቷ እድገት በአንድነት እንዲሳተፉ ያደርጋቸዋል። ወደፊትም በዚሁ ልማድ
ሁሉም መሳተፍ እንዳለበት እናምናለን።

7) የዚህ ጽሁፍም ሆነ የብዙዎች ፍላጎት፤ ሁላችን በፍቅር ተሰባስበን ፈጣሪያችንን ለማመስገንና ቤተክርስቲያናችንን ለማሳደ
ግ እስከሆነ ድረስ ፤ ለሰበካ ጉባኤ አባልነትም ሆነ ለንዑሳን ኮሚቴዎች የሚመረጡ አባላት ሰላማዉያንና ሁሉን በእኩል አ
ይን የሚያዩ ለአንድነት ጠንክረዉ የሚሰሩ መሆን ይኖርባቸዋል። ስለዚህ ለሰላም መስፈን የሚመረጡት ሰዎች በማህበረ ም
እመናኑ ተጠቁመዉ ሊመረጡና ፤ ከማንም ወገን አስተሳሰብ ተጽእኖ ነጻ የሆኑና ፤ ለፍቅር ፣ ለሰላም መስፈን የሚተጉ ሊሆ
ኑ ይገባል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መፍትሔ ኃሳቦች ለቤተክርስቲያናችን ዘላቂ ሰላምን ሊያመጡ ይችላሉ በማለት የተዘረዘሩ ናቸዉ።
ይሁን እንጂ በለንደን የምትገኘዉ ቤተክርስቲያናችን በጣም ወቅታዊ የሆነ ችግር ገጥሟታል። የስራ ጊዜዉን ሊያጠናቅቅ የ
ተቃረበዉ የሰበካ ጉባኤ አስተዳደር  የቤ/ክኗ ሀብትና ንብረት እንዳይባክን የተለመደዉን አሰራር አስወግዶ በሕግ ጥላ ስር
ለማስኬድ የ2002  (እ.አ.አ) የደብሩ በጀት እንዲጠና አድርጎ ገቢዉን ከወጪዉ ጋር በማጣጣም በጉባኤዉ አባላት የታመነበ
ትን (ራሳቸዉ ቄስ ብርሃኑም የፈረሙበት) በጀት በቤተ ክርስቲያኗ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ መልክ ካጸደቀ በኋላ በ
ተለይ የካህናትን አበል ለመደልደል ሲዘጋጅ በቄስ ብርሃኑ ብስራት የተነሳ ከፍተኛ የሆነ ችግር ገጥሞታል።  የችግሩ መነሻ
ም፤

1ኛ/ በ2000 ዓ.ም በሰበካ አስተዳደር ጉባኤ እና ቄስ ብርሃኑ ባደረጉት የጓዳ ስምምነት የቤ/ክኗ የስእለት ገንዘብ ገቢን ከወ
ጪ ሳያመዛዝን በአንድ ጊዜ ከ240 ወደ 600 ፓዉንድ እንዲከፈል የ1 ዓመት ኮንትራት በስዉር ካህናትም ሆነ ምእመናን ሳ
ያዉቁት ተፈርሞ በመቆየቱና በአሁኑ ሰዓትም የኮንትራት ጊዜዉ አልቆ በይገባኛል ባይና በአስተዳደር ጉባኤዉ መሐከል ዉ
ጥረት አስከትሏል። በመሠረቱ ከቤ/ክኗ የገቢ አቅም፣ እንዲሁም የራሳችንን ሕንጻ ለመግዛት ካለን ብርቱ ፍላጎት ካህናት በ
አበል መልክ ይከፈላቸዉ ነበር እንጂ በቅጥር ሆኖ አያዉቅም።  ይሁን እንጂ እስከዛሬ ያልነበረ ይህን የቅጥር ዉል ሲፈረ
ም የሰበካዉ ጉባኤ ማንንም ሳያማክር በራሱ ፈቃድ የቻሪቲዉ ሕግን በመጣስ ቃለዓዋዲዉን የሚያዘዉን በመተዉ (አንቀጽ 1
2 ቁጥር 14) አለ በጀት ቄስ ብርሃኑን ቀጥሯል። ይህን ሕግ ብቻ አይደለም የተጣሰዉ፣ በአንቀጽ 59 ቁጥር 4 ላይ ስለቅጥር
የተጠቀሰዉን (....የጠባይና የሥራ ችሎታ መመዘኛ ሥራዉንና ቦታዉን በመጥቀስ በይፋ ማስታወቂያ አዉጥቶ በማወዳደር መ
ምህራንን፣ሰባክያንን፣ ቀሳዉስትን፣ ዲያቆናትን፣ መዘምራንን ሊቀጥር የሚችለዉ በወረዳዉ ቤተክህነት ኃላፊነት ይሆናል።)
ከምንም አልቆጠረዉም። ከሁሉም በላይ ደግሞ የተጣሰዉ በዚሁ አንቀጽ 59 ቁጥር 5 ላይ የተጠቀሰዉ ነዉ.........በሀገረ ስብ
ከቱ በኩል በፈተና ተወዳድረዉ የሚያልፉት ብቻ ከሚላኩላቸዉ በስተቀር በአጥቢያዉ አስተዳዳሪ ወይም በሰበካ ጉባኤ ሥ
ልጣን ማንኛዉም ቅጥር ሊፈጽም አይችልም። ሀገረ ስብከቱ በዚህ ለጊዜዉ በአዉሮፓ ስላልተቋቋመ የክህነትን ቅጥር በተ
መለከተ የካህናት ጉባኤን ይመለከታል እንጂ የክህነት ትምህርት የሌላቸዉ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አባላት ፈትነዉ ለመቅ
ጠር አይችሉም፣ አያስኬድም።

ከላይ እንደተገለጸዉ <u>ቄስ ብርሃኑ ተቀጠሩ የሚባለዉ ለ1 ዓመት ኮንትራት ነዉ</u>። ይሁን እንጂ ይህ ኮንትራት ካለቀ በኋላ ከ
ቤ/ክኗ የበጀት አቅም አኳያ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የመደበላቸዉን አበል 240 ፓዉንድ ለመቀበል ፈቃደኛ ሆ
ነዉ ባለመገኘተቸዉ እና ጉዳዬን በጥልቅ ሳልተረዱ ሰዎች የተበደሉ አስመስለዉ በማቅረብ ቤ/ክኗ ሰላም እንድታጣ ማድረ
ጋቸዉን ቀጥለዉበታል።  አድማ በመቀስቀስ ጉባኤዉ በቀረዉ የሥራ ጊዜ አገልግሎት መስጠት እንዳይችል እንቅፋትም ሆነ
ዋል። በየትኛዉም መ/ቤት አንድ ሰዉ የኮንትራቱ ጊዜ ሲያልቅ ካስፈለገ ይታደሳል ያለበለዚያ ይሰናበታል ወይም ደግሞ የኮ
ንትራት ዉሉ እንዳስፈላጊነቱ ተሻሽሎ ይፈረማል እንጂ ሌላ መ/ቤት ቢሆን የማያደርጉትን ተሰምቶ የማይታወቅ <u>600 ፓዉ
ንድ ካልተሰጠኝ ቤ/ክኗን አበጠብጣለሁ</u> ማለት፤ ለሕግ አልገዛም ማንንም አልፈራም ማለት ህዝብን ከመናቅ የሚቆጠር ነዉ
።

በሰኔ 16፣2002 እ.አ.አ በተካሄደዉ የዓመታዊ ሪፖርት ማሰሚያ ላይ ቄስ ብርሃኑ በዉጭ አስተባብረዉ ይዘዋቸዉ የመጢቸዉን ሰዎች በመተማመን እስብሰባዉ ላይ ከዚህ በፊት በስብሰባ ሥርአት ሆኖ የማያዉቀዉን ደሞዜን ካልጨመራችሁ ብለዉ ኡኡታ አሰምተዉ ነበር። ይህ ከሥርአት ዉጭ የተነሳ ጥያቄ ሊቀመንበሩ ማስቆም ሲገባቸዉ እንዲያዉም ከስብሰባ እየወጡ የነበሩትን እስከበሩ ድረስ እየተከተሉ እባካችሁ ተመለሱና ድምጽ ስጡ ሲሉ ለተመለከተ የሚያስገርም ነበር። ከዚያ አልፎም ድምጽም የቆጠሩት ራሳቸዉ ነበሩ። የተመዘገቡ የቤ/ክኗ አባላት ብዛትም 700 የሚደርስ መሆኑ እየታወቀ የቄስ ብርሃኑ ደመወዝ ይጨመር ብለዉ የወሰኑት 34 ሰዎች ነበሩ። ከሁሉ የሚገረመዉ ድምጽ ከሰጡት መሀከል አንዳንዶቹ እዚያዉ አደባባይ ላይ የአባልነት ክፍለን እናዉቅም በማለት እየተናገሩ ድምጻቸዉ መቆጠሩ ነዉ። ይህ ደግሞ በቃለ አዋዲዉ ሆነ በቻሪቲ ኮሚሽን ላይ የተደነገገዉን (......ድምጽ መስጠት የሚችሉት የተመዘገቡና ክፍያ ያሟሉ አባላት ብቻ ናቸዉ የሚለዉን....) የሚጻረር ነዉ። እንዲሁም ደግሞ ሕጉ እንደሚያዘዉ በስብሰባዉ ላይ የተገኙት የአባልነት ክፍያ ያሟሉ ይሁኑ አይሁኑ ለማወቅ ስም ዝርዝርም አልተያዘም። በማንኛዉም እንደዚህ ያለ ስብሰባ ላይ አጠቃላይ የመንፈሳዊ ጉባኤ በጀት ይጨመር ወይ ይቀነስ ይላል እንጂ በአስተዳደር ሥራ ገብቶ የሠራተኞች ደመወዝ በይህን ያህል ይጨምር አይልም። ማንኛዉንም ዉሳኔ ለማሳለፍ ደግሞ 2/3ኛ የአባለት ድምጽ ያስፈልጋል እንጂ ጥቂት ተመካክረዉ የመጡ ሰዎች በማን አለብኝነት የመወሰን መብት እንደሌላቸዉ በሕጉ ላይ በግልጽ ተጽፏል። ይህ ለወደፊቱም ሊታወቅ ይገባል። ስለዚህ በዚያን ቀን የቄስ ብርሃኑ ደሞዝ ይጨመር ብሎ የተወሰነዉ ተቀባይነት አይኖረዉም።

ይሁን እንጂ የዚያኑ ቀን (በሰኔ 16፣2002 እ.አ.አ) ለቤ/ክኗ ሰላም ሲባልም ችግሩን የተረዱ ካህናት ለሰላም ሲሉ የትራንስፖርት አበሉ ከሌሎች ካህናት እኩል እንዲከፈላቸዉ እና ቀረብኝ የሚሉትን ገንዘብ ለእነሱ የተመደበዉን ገንዘብ ተጨምሮ እንዲሰጣቸዉ በማለት ለግሰዋል። ይሁን እንጂ በሐምሌ 14፤2002 እ.አ.አ በተካሄደዉስበሰባ ላይ ግን የሌሎቹ ሳይጓዋደል ቄስ ብርሃኑ ቀረብኝ የሚሉትን ገንዘብ የተለያየ የስራ ዝርዝር ወጥቶለት በዚያ መሠረት ይከፈላቸዉ ተብሎ ለቀረበዉ መፍትሔ ኃሳብ ተገዢ አልሆንም፣ እንዲያዉም ሕግም የምትሉት ቢወጣ እኔን አይመለከትም እስከ ማለት ደርሰዋል። ካህናቱ ያቀረቡት ኃሳብ ቄስ ብርሃኑ እንደሌላዉ ካህናት የተመደበዉን እያገኙ ተጨማሪ ስራ ተሰጥቷቸዉ የጠየቁት ገንዘብ 512 ፓዉንድ ይሰጣቸዉ ነበር። በጣም የሚገርመዉ ግን ቄስ ብርሃኑ ከሌሎቹ የተለየ ሌላ ተጨማሪ ሥራ አልሰራም ግን የሳቤን ዋጋ 600 ፓዉንድ ለእኔ፤ ለሌሎቹ ደግሞ የተመደበላቸዉን (200 ፓዉንድ) ያግኙ የሚል ነዉ። በእኝሁ ቄስ የተነሳ የሰ/መ/አ/ጉባኤ አባላት መግባባት ሰላልቻሉ ጉዳዩን እንዲመለከቱ የተለያዩ ንዑሳን ኮሚቴዎችን በ10 ነሐሴ 2002 እ.አ.አ ሰብስበዉ እነዚህ አባላት የሚወስኑትን ሊቀበሉ ቃል ገብተዉ ዉይይቱ ተጀምሮ በሳምንቱ በ17 ነሐሴ 2002 ዉሳኔ ኃሳብ አሳልፏል። ዉሳኔዉም ቄስ ብርሃኑ የጠየቁትን 512 ፓዉንድ በተለያየ የሥራ ድርሻ ለሰላም ሲባል እንዲሰጣቸዉ ሆኖ ነገር ግን አድልዎ የሌለበት ለማድረግ ሲባል እንደሌሎች ካህናት የቅስና መደብ 200 ፓዉንድ ላይ ተጨማሪ ሥራዎችን ተዘርዝረዉ ከነክፍያቸዉ ያግኙ ብሎ ወስኗል። ይሁን እንጂ በ26 ነሐሴ 2002 እ.አ.አ የሰ/መ/አ/ጉባኤ ባደረገዉ ስብሰባ ላይ ነገር የማይታከታቸዉ ቄስ ብርሃኑ ዉሳኔዉን እንደማይቀበሉ እንዲያዉም ከመችዉም ጊዜ በበለጠ ኃይለ ቃል ይህቺን ቤ/ክን እንድትበጠበጥ አደርጋለሁ ብለዋል።ቀጣሪ ነን ባዮቹ የንዑሳን ኮሚቴዎችን ዉሳኔ አንቀበልም ብለዉ እናስፈጽማለን ያሉት ቃላቸዉን አጥፈዋል።

ለቤ/ክኗ ሰላምና እንዲሁም ቄስ ብርሃኑን ለማስደሰት የቀረበዉን ይህን መፍትሔ ኃሳብ አሁንም ቄስ ብርሃኑ አለመቀበላቸዉ ፍጹም ትዝብት ላይ የሚጥላቸዉና ምን ዓይነት ሰዉ እንደሆኑ በግልጽ ያስረዳል። የካህናት ጉባኤዉም ሆነ ለሎች ለሰላም የተነሳሱ ምእመናን ለሰላም ሲሉ ከሕግ ዉጭ ሄደዋል ባዮች ነን። ምክኒያቱም ከዚህ በፊት የተወሰኑ ሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አባላት የሰሩትን ስህተት አሁንም እየደገሙ ነዉና፤ ማለትም ብዛት ያላቸዉ ካህናት በቤ/ክኗ እያሉ ተጨማሪ 3 የሥራ መደብ ለአንድ ሰዉ መስጠት አድሎአዊ ያሰኛል። ሕግ ሁል ጊዜ እየተጣሰ መኖር ስለሌለበት ከአሁን ጀምሮ በሥርዐቱ ልንመራ ይገባል። ቃለ አዋዲዉ በአንቀጽ 59 ቁጥር 4 ላይ ስለቅጥር የተጠቀሰዉን መሠረት በማድረግ ለተጨማሪዎቹ 3የሥራ ቦታዎች ማስታወቂያ ወጥቶ ቄስ ብርሃኑም እንደሌላዎቹ ተወዳድረዉ ሊከፈላቸዉ ይገባል እንጂ ቄስ ብርሃኑ እንደሚሉት« ሁልጊዜ ለእኔ የተለየ መሆን አለበት» ማለት ራሰ ወዳድነትን የሚያሳይ ፍጹም ክርስቲያናዊ ያልሆነ መንፈስ ነዉ። የተሰጣቸዉን አልቀበልም ካሉ ግን የግድ በገንዘብ ቤ/ክኗን እንዲያገለግሉ ሰላልተባሉ የመተዉ መብት እንዳላቸዉ ልናስገነዝባቸዉእንወዳለን። ነገር ግን ለግል ጥቅማቸዉ ሲሉ የቤ/ክኗን ሰላም እነሳለሁ የሚሉ ከሆነ እኝህን ሰዉ ከቤ/ክኗ እንዲወገዱ ያስፈልጋል እንጂ እሹሩሩ እየተባሉ ሊኖሩ አይገባም። ይህ ሁሉ ጥረት በመደረግ ላይ ያለዉ ማንም ሰዉ ከዚህ ቤተክርስቲያንእንዳይርቅ በማለት እንጂ እንደ ቄስ ብርሃኑ ብሥራት ምግባርማ ቢሆን መባረር የሚገባቸዉ ከዓመታት በፊት ነበር። ሰላምለማምጣት ይህ ሁሉ እየተጣረ ሳለ ቄስ ብርሃኑ ብሥራት ቤ/ክኗንም በሕግ በኩል እየከሰሱ ስለሆነ የሚያዋጣቸዉ ከሆነ በዚያዉ በክሱ እንዲቀጥሉበት ሆኖ ከአሁን በኋላ ግን እሳቸዉ እንደሚያስቡት ሕግ እስኪፈርድላቸዉ ከሥራ እንዲታገዱ ወይም እንደሌሎች ካህናት እኩል የሚሰጣቸዉን እየተቀበሉ በሰላም አብረዉ እንዲኖሩ እናሳስባለን።

እንዲያዉም በአዲስ መልክ የቤ/ክኗ አስተዳዳሪ ነኝ የሚል ጥያቄ በማቅረብ ቤ/ክኗን የበለጠ ለመበጥበጥ ሆን ብለዉ ተነስተዋል። ቄስ ብርሃኑ ብስራት እንኳን ለአስተዳዳሪነት ይቅርና ለቅዳሴዉ አገልግሎት እንኳ ገና ብዙ የሚቀራቸዉ ፣ በፈገግታ፣ በረጅም ምላስና ቀሚስ ራሳቸዉን ደብቀዉ፣ መልሕቁን የሚጥልበትን እንዳጣ መርከብ እየተንገዋለሉ ከእንደበታቸዉ በሚወጣዉ አስጸያፊ ቃላት ቤ/ክኗን ከችግር ለመጣል ቆርጠዉ የተነሱ በመሆናቸዉ እዉነተኛ የሆናችሁ በሙሉ ይህን በሚገባ ተረድታችሁ፤ ለእምነታችሁ ስትሉ ጉዳዩን በቅርብ በመረዳት የማያዳግም መፍትሄ እንድትሰጡ ጥሪ ቀርቦላችኋል።

ቤተክርስቲያናችን እንድታድግ፣ ወንጌል መንግስት እንዲስፋፋ ፣ በፍቅር እንድንኖር ከተፈለገ ፤ ሁላችንም የተደቀኑብንን ችግሮች ጊዜ ሰይሰጡ በየጊዜዉ በመገናኘት ፍጹም በሆነ መንፈሳዊ ፍቅር ፤ በመከባበር ፤ ተወያይቶ መፍታት ከእያንዳዳችን ይጠበቅብናል። ያለንበት ቦታ መንፈሳዊ እስከሆነ ድረስ ፤ይህ የምናደርገዉ ጥረት ደግሞ ከአምላካችን ዘንድ በረከት እንደሚያስጠን እምነን ፤ ሕይወታችንን እንደ ሕጉ «...እርስ በርሳችን ልንዋደድ......» ይገባል፤ በሚለው መመሪያ ከራሳችን

ይልቅ ለሌላው ሰላም የሚያመጣ፣ ከግለሰብ ይልቅ ለኃጢአታችን ስለ ሞተው ስለ ጌታችን መመስገኛ ቤት ቅድሚያ ሰጥተን ለተቀደሰ ተግባር እንድንዘጋጅ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

እግዚአብሔር አምላካችን ለቤተክርስቲያናችን ፣ ለሀገራችን ሰላሙን ፣ ፍቅሩን ፣ በረከቱን ያድልልን።

ግልባጭ፤
ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት
ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት
ለደብረ ጽዮን ቅ/ማ/ቤ/ክን አባላት በሙሉ
ለጽርሃ ጽዮን ቅ/ማ/ቤ/ክን ሰ/መ/አ/ጉባኤ ጽ/ቤት ለንደን
ለብጹዕ አቡነ ቀዉስጦስ
ለብጹዕ አቡነ ሰላማ
ለብጹዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ
ለብጹዕ አቡነ ኢሳይያስ
ለብጹዕ አቡነ ቄርሎስ
ለብጹዕ አቡነ ገብርኤል
ለብጹዕ አቡነ አትናቴዎስ
ለእንጦጦ መንበረ ሥላሴ ቤ/ክ ሰ/መ/አ/ጉባኤ ጽ/ቤት
ለኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክን በሆላንድ
ለኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክን በጀርመን
ለኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክን በስዊትዘርላድ
ለኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክን በግሪክ
ለኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክን በጣሊያን
ለኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክን በስዊድን
ለኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክን በአሜሪካ
ለኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክን በካናዳ

በተጨማሪ ኢትዮጵያ ለሚገኘዉ ለሩህ መጽሔት አጠር ባለ መልኩ «የለንደንን ደ/ጽ/ቅ/ቤተክርስቲያን በማመስ ላይ የሚገኙት ቄስ ብርሃኑ ብሥራት እናስተዋዉቃችሁ» በሚል ርእስ የሀገራችን ሕዝብ ችግራችንን እንዲረዳዉ እንዲሁም በጸሎት እንዲያስብዎ በማሰብ በማለት የተላከ መሆኑንና በኢንተርኔት ላይም እንዲወጣ የምናደርግ መሆኑን አስቀድመዉ እንዲያዉቁት።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።
ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክ ማህበረ ካህናት እና ምእመናን በሙሉ

በለንደን የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የደ/ጽ/ቅ/ማርያም ቤ/ክ በመምሬ ብርሃኑ ብሥራት አማካይነት የደረሰባትን ችግር አንብቦ በመረዳት እያንዳንዱ በእምነቱ አስገዳጅነት ለማንም ሳይል መፍትሄ እንዲፈልግ ጥሪ ለማቅረብ የወቅቱ አስገዳጅ ሆኗል።

በመሠረቱ በአጸደ ነፍስ ያሉት ብጹእ አቡነ ዮሐንስ ካረፉበት ዕለት አንስቶ አሁን እስካለንበት 5 ዓመታት ድረስ መምሬ ብርሃኑ ብሥራት የስዕለቱን ገንዘብ ከአስተዳዳሪነቱ ጋር ተጣምሮ ለብቻዬ ይሰጠኝ በማለት በቤ/ክኗ ላይ የሚያካሂዱት የከፋፍለህ ግዛዉ ዘመቻ በዚህ ጊዜ ያበቃል ከማይባልበት ደረጃ ላይ በመድረሱና እስከመጨረሻይቱ ሕቅታ ድረስ መበጥበጤን አላቆምም ስላሉ ምንም እንኳ ታሪኩ በተከታታይ እትም የሚገለጽ ቢሆንም ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀዉን አይታችሁ ህዝቡን አበትናለሁ ፣ ቤ/ክኗን እከፍላለሁ ከሚሉ የገንዘብና የሹመት ፍቅር ልቦናቸዉን ካደነደነዉ ቁስ ቤ/ክኗን አስቀድሙና ፈጥናችሁ ድረሱላት።

እስካሁን እንዳየነዉ አዳም 5500 ዘመን በሲኦል ከተቀበለዉ መከራ የለንደን ደ/ጽ/ቅ/ማ ቤ/ክ በዚህ 5 ዓመታት ዉስጥ በመምሬ ብርሃኑ ብሥራት አማካይነት የደረሰባት ችግር የሚያመዝን ነዉ። ትንቢቱ ሲደርስ ቃል በማሕፀን ቅድስት ድንግል ማርያም ተጸንሶ በመወለዱ አዳም ድህነት አግኝቷል።

የመምሬ ብርሃኑ ብሥራት ግን ትንቢትም የሌለዉ በዚህ ዘመን ያስተዉላሉ የማይባሉ ፤ ለበጎች ሲሉ ራሳቸዉን መግዛት እስኪችሉ ቢመከሩም ልቡናቸዉ ደንድኖ አልመለስ በማለታቸዉ ጊዜ ተርፎት ከሳቸዉ ጋር እዉነቱን እያዩ እንዳላዩ በመሸፋፈን ሁከትና ብጥብጥ መቀስቀስ ከሚፈልጉ ሰዎች ጋር ነጥብ በሌለዉ ጭቅጭቅ መቆየትን የሚፈልግ ባለመኖሩ ከአሁን በኋላ ፍትሕ ፣ ርትእ በቤ/ክን ዓዉደ ምህረት ይጀመር የምትሉ ሁሉ እዉነተኛዉን መልእክት ተረድታችሁ ወደ አንድነት የሚያመጣ መፍትሄ እንድትፈልጉ አደራ እያልን በሚቀጥለዉ እትም 1ኛ/ ወፌ ገዝቱ ቁስ 2ኛ/ አብሮ ያደገ ግብር በማስረጃ የተደገፈ 3ኛ/ ሹመትና የገንዘብ መዉደድ ከቤ/ክኗ አባባል ጋር የሚቃረኑበት ምክንያት 4ኛ/ እኔ ከምትኩ ሰርዶ አይብቀል 5ኛ/ ሰዉ ለተሸነፈበት ነገር ባርያ ነዉ 6ኛ/ በርታ ግፋ እኛ እንጩህልሃለን የሚሉትን እና ለወደፊቱም በሂደት የሚከሰቱትን በተከታታይ ጽሁፍ ስለምናቀርብ ሁላችሁም ይህን እየተመለከታችሁ የቤ/ክኗ ሰላም ሊገኝ የሚችልበትን መንገድ እንድትፈልጉ በእግዚአብሔር ስም አደራ እያልን ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን 19 ገጽ እንዲደርሳችሁ አደርገናል።

ሰላም ለኢትዮጵያ፣ ሰላም ለቤተክርስቲያን ፣ ሰላም ለዓለም ሁሉ

ከእውነት ማህደር